# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 059 ጥቅምት 29 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









## መገናኛ ብዙኃን ለውጤታማ ሀገራዊ ምክክር

ገጽ 4









# የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አራት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸው ምርቶችን አገበያየ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በ2016 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት አራት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸው የተለያዩ ምርቶችን እንዳገበያየ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አስታወቀ።በዘንድሮ በጀት ዓመት 37 ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸው ምርቶችን ለማገበያየት ታቅዷል።

በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገበያና ግብይት ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ በኃይሉ ንጉሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ምርት ገበያ በሩብ ዓመቱ አምስት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸውን 53 ሺህ 236 ሜትሪክ ቶን የተለያዩ ምርቶችን ለማገበያየት አቅዶ ሲሠራ ቆይቷል፡፡ በሩብ ዓመቱ ያሳካው አራት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸውን 39 ሺህ 324 ሜትሪክ ቶን የተለያዩ ምርቶችን ግብይት ነው።

ግብይት ከተፈጸመው 39 ሺህ 324 ሜትሪክ ቶን ውስጥ ከፍተኛውን መጠን የሚወስዱት ምርቶች ቡና፣ ሰሊጥና ነጭ ቦለቄ መሆናቸውን አቶ ኃይሉ አብራርተዋል።

የተጠቀሱት ምርቶች ከሩብ ዓመቱ አጠቃላይ

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ...ወደ ገጽ 14 ዞሯል



ፎቶ - አዩብ ተፈሪ

# «አካዳሚው በአህጉር ደረጃ የአመራር ችግርን ለመፍታት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጀምሯል»

- አቶ ዛዲግ አብረሃ

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ርዕሰ አካዳሚ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- አካዳሚው በአፍሪካ አህጉር ደረጃ ያለውን የአመራር ችግር ለመፍታት የሚያስችል ተግባራዊ እንቅስቃሴ መጀመሩን የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ርዕሰ አካዳሚ ዛዲግ አብረሃ ተናገሩ፡፡

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚና ከቻይና ብሔራዊ አስተዳደር አካዳሚ ጋር አብሮ ለመሥራት

«አካዳሚው በአህጉር ደረጃ... ወደ ገጽ 14 ዞሯል



ወ/ሮ ደርጋሰም ጥላሁን

# ትርጉም የሚያስፈልጋቸው 10 መዝገቦች ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ተልከዋል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሦስት ወራት ከተመለከታቸው 504 መዝገቦች መካከል የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልጋቸው 10 መዝገቦችን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት መላኩን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ

ትርጉም የሚያስፈልጋቸው... ወደ ገጽ 14 ዞሯል









## «ኢትዮጵያ ለዳታ ማዕከላት ልማት ትኩረት ሰጥታ እየሠራች ነው»

- በለጠ ሞላ (ዶ/ር)
የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር

**ተስፋ ፈሩ**

አዲስ አበባ፡- ዲጂታል ትራንስፎርሜሽንን እውን ለማድረግ ለዳታ ማዕከላት ልማት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) ገለጹ።

የዳታ ማዕከላትን ለፋይናንስ ዘርፍና ለአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ጅማሮ ማዋል የሚቻልበት ሁኔታ ላይ ያተኮረ ውይይት ባለድርሻ አካላትና ከፍተኛ የመንግሥት አመራሮች በተገኙበት ትናንት ተካሂዷል።

በውይይቱ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትሩ በለጠ ሞላ (ዶ/ር) ኢትዮጵያ የዳታ ማዕከላትን ለማልማት ከተለያዩ አካላት ጋር እየሠራች መሆኑን ገልፀዋል። ለአብነትም በአራት አፍሪካ ሀገራት ውስጥ አገልግሎት እየሰጠ ያለው ዊንጉ አፍሪካ በአይሲቲ ፓርክ ውስጥ ኢንቨስት ማድረጉን ጠቅሰዋል።

ኢትዮጵያ የዲጂታል ኢኮኖሚ ሽግግሩን የሚያፋጥኑ የዳታ ማዕከላትን ወደ ሥራ ማስገባቷን አስታውቀው፤ ባለፉት ሦስት ዓመታት በርካታ የዳታ ማዕከላት ግንባታ የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች እየቀረቡ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ጉባኤውን «ወቅቱን የሚዋጅና በጣም አስፈላጊ» ሲሉ የገለጹት ሚኒስትሩ፣ የአይሲቲ ፓርክ ኮርፖሬሽን በኢትዮጵያ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጉዞ ላይ ቁልፍ ሚና መጫወት የሚያስችል እምቅ አቅም አለው ብለዋል።

የዳታ ማዕከል አገልግሎት አቅራቢዎችንና ሌሎች ዲጂታል ኢንቨስትመንቶችን ለመሳብና ለመደገፍ ጠንክሮ እየሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

የአይ ሲቲ ፓርክ ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሄኖክ አህመድ በበኩላቸው፤ የግሉ ዘርፍ በዳታ ማዕከላት ልማት እንዲሳተፍ ምቹ ሁኔታዎች መፈጠራቸውን ገልፀው፣ ከዊንጉ አፍሪካ በተጨማሪም በቀጣይ ወደ ገበያው የሚገቡ መሰል የዳታ ማዕከላት በሂደት ላይ መሆናቸውንም ጠቅሰዋል።

በዓለም ደረጃ የዳታ ማዕከላትን ገንብቶ አገልግሎት ለሚፈልጉ ተቋማት ማቅረብ የተለመደ መሆኑን የጠቆሙት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ «ሌሎች ተቋማት የዳታ መሠረተ ልማት መገንባት ሳያስፈልጋቸው ዋና ሥራቸው ላይ አተኩረው በመሥራት አገልግሎቱን የሚያገኙበትን ዕድል ይፈጥራል። የፋይናንስ ተቋማትም በዚሁ መሠረት የራሳቸውን ዳታ ማዕከል መገንባት ሳያስፈልጋቸው አገልግሎት ያገኛሉ» በማለት በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት የሀብት ውስንነት ስላለ ያለን ሀብት በመጋራት መጠቀም ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

# ከቡና የሚገኘውን ገቢ ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ለማድረስ እየተሠራ ነው

**ታደሰ ብናልፈው**



አዲስ አበባ፡- በቀጣይ ሁለት ዓመታት ከቡና የሚገኘውን የወጪ ንግድ ገቢ ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ለማድረስ እየተሠራ ነው ሲል የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን የሕዝብ ግንኙነትና የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሳህለማርያም ገብረመድህን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን የቡና ምርት ጥራት በተሻለ መልኩ በማቅረብና ንግዱን ወደ ተለያዩ ሀገራት በማስፋፋት ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ለማድረስ እየተሠራ ነው።

ባለፈው በጀት ዓመት ከ240 ሺህ ቶን በላይ ቡና ወደ ሳዑዲ ዐረቢያ፣ ጀርመን፣ አሜሪካ፣ ኮሪያ፣ ቤልጅየም፣ ጃፓን እና ዩናይትድ ዐረብ ኢምሬትስ ሀገራት በመላክ አንድ ነጥብ 34 ቢሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን አንስተዋል።

በተያዘው በጀት ዓመት 350 ሺህ ቶን ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ አንድ ነጥብ 75 ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ተቋሙ በመጪዎቹ ሁለት ዓመታት ከቡና የወጪ ንግድ የሚያገኘውን ገቢ ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ለማድረስ እየሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

በቀጣይ ሁለት ዓመታት ገቢውን ሁለት ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ በዘርፉ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን ማለትም የቡና ግብይት፣ ጥራት፣ ብክነትና የጣዕም ደረጃ ዙሪያ ያለውን ችግር ለመፍታት የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የቡና ምርትን ጥራት በመጠበቅና በማሻሻል ከወጪ የሚገኘውን ዶላር ለማሳደግ ለአርሶ አደሩ የግንዛቤ ማስጨበጥ ትምህርት የመስጠት፣ ድጋፍና ክትትል የማድረግ ሥራ እየተሠራ ይገኛል ሲሉ አብራርተዋል።

በአብዛኞቹ ቡና አምራች አካባቢዎች የሚገኙት የቡና ዛፎች ያረጁ በመሆናቸው ምርትና የምርት ጥራታቸው ቀንሷል፤ ይህን የቡና ጥራት ችግር ለመፍታት የቡናን ምርት ለማሳደግ ያረጁ የቡና ዛፎችን የማደስ ሥራ እየተሠራ ነው፤ እየተሠራ ባለው ሥራ እስካሁን ወደ 400 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የሚገኙ የቡና ዛፎች ተጎንድለዋል ሲሉ ገልጸዋል።

የቡና ምርትን በብዛትና በጥራት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ከምርምር ተቋማትና ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በቅርበት እየተሠራ ከመሆኑም በተጨማሪ የተሻሻሉ ዝርያዎችን ለአርሶ አደሩ የማቅረብ ሥራ እየተከናወነ ነው ብለዋል።

በቀጣይ ሁለት ዓመታት ከወጪ የቡና ንግድ ለማግኘት የታቀደውን ሁለት ቢሊዮን ዶላር ለማሳካት በግብይቱ የሚታዩ ተግዳሮቶችን የመፍታት ሥራ ከወዲሁ እየተሠራ ነው ሲሉ አመላክተዋል።

# ሚኒስቴሩ ያስማቸው ሦስት የቴክኖሎጂ ሥርዓቶች የዲጂታል ስትራቴጂውን ለማሳካት ያግዛሉ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ሚኒስቴሩ ያለማቸው ሦስት የቴክኖሎጂ ሥርዓቶች እንደሀገር የተጀመረውን የዲጂታል ስትራቴጂ ለማሳካት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል አስታወቁ፡፡

ሚኒስቴሩ ከአጋር ተቋማት ጋር በመተባበር ያለማቸውን ሦስት የቴክኖሎጂ ሥርዓቶች ትናንት አስመርቆ ወደሥራ ባስገባበት ወቅት ንግግር ያደረጉት ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል፤ ቴክኖሎጂዎቹ እንደ ሀገር የተቀመጠውን የዲጂታል ኢትዮጵያ ስትራቴጂ ለማሳካት ጉልህ ሚና ይኖራቸዋል ብለዋል፡፡



ፎቶ ገባቦ ገብሬ

ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል

ወደሥራ ከገቡት የቴክኖሎጂ ሥርዓቶች መካከል በጥንታዊ የኢትዮጵያ ቅርስ ሉሲ (lucy) ስም የተሰየመውና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የገበያ ችግር ለመፍታት የሚረዳው የቴክኖሎጂ ሥርዓት አንዱ መሆኑን ገልጸዋል።

የሉሲ ቴክኖሎጂ ሥርዓት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የግብይት ሥርዓት የሚያዘምንና የተሻለ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል መሆኑን አስታውቀዋል።

በተጨማሪ ለኢንተርፕራዞቹ የምርት መሸጫ ቦታ፣ ወደ ታክስ ሥርዓት እንዲገቡ የሚያስችል ሥርዓት፣ በውጭና በሀገር ውስጥ ገበያ ዕድል የሚፈጥር እንዲሁም ፍትሐዊ ተደራሽነት የሚያረጋግጥ ሥርዓት መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ሁለተኛው የቴክኖሎጂ ሥርዓት ደግሞ ሲኦሲ (coc) የተሰኘው መሆኑን አመላክተው፤ ቴክኖሎጂው በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የሚስተዋለውን የሐሰተኛ ማስረጃዎችን ችግር ለመፍታት የሚያችል ነው ብለዋል።

ወደአገልግሎት የገባው የሲኦሲ ቴክኖሎጂ ሥርዓት እውን እንዲሆን የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት በዋናነት መሳተፉን ጠቁመው፤ ቴክኖሎጂው በዘርፉ ትልቅ ሽግግር የሚፈጥር መሆኑን ተናግረዋል።

ሦስተኛው የቴክኖሎጂ ሥርዓት ደግሞ ብቁ (BEQU) የተሰኘ የሞባይል መተግበሪያ ሲሆን፤ በሥራ ዕድል ፈጠራ የሥራ ልምምድ ላይ ውጤታማ ሥራ ለማከናወን የሚረዳ ሥርዓት መሆኑን አስታውቀዋል።

የቴክኖሎጂ ሥርዓቶቹንና በማልማት ሂደቱ የኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲቱትና የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አገልግሎት ትልቁን አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ወርቁ ጋቸና በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ኢንስቲትዩቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ሥራዎችን ሲሠራ ቆይቷል፤ በተለይም ሀገሪቱ በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ቴክኖሎጂ ግንባር ቀደም የሚያደርጋትን ተቋም እውን ለማድረግ እየተሠራ ነው፡፡

ወደሥራ የገቡት ሦስቱ የቴክኖሎጂ ሥርዓቶች ተቋሙ ካከናወናቸው ሥራዎች ጥቂቶቹ ናቸው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ሥርዓቶቹ የዜጎችን የኑሮ ሥርዓት የሚያቀሉና በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚረዱ ናቸው ብለዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ 21 የቴክኖሎጂ ሥርዓቶች ልማት ላይ ሲሠራ መቆየቱ ተገልጿል።



ኮሚሽነር አይሻ መሐመድ

## ክልሉ ሦስት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ላስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሰጠ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፦ በ2016 በጀት ሩብ ዓመት ሦስት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠቱን የአፋር ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

የአፋር ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር አይሻ መሐመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የኢንቨስትመንት ዘርፉን ለማነቃቃት በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛል፡፡

በ2016 በጀት ዓመት ለ210 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ፤ በሩብ ዓመቱ ሦስት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ 36 ባለሀብቶች ፈቃድ መሰጠቱን አመላክተዋል።

ፈቃድ የወሰዱት ባለሀብቶች በእርሻ፣ በሆቴል፣ በኢንዱስትሪ እና ኮንስትራክሽን ዘርፎች ላይ የተሰማሩ መሆናቸውን ገልጸው፤ በእርሻ ለተሰማሩ ባለሀብቶች ስድስት ሺህ ሄክታር መሬት ተላልፏል ብለዋል፡፡

ፈቃድ የወሰዱ ባለሀብቶች በሙሉ አቅማቸው ወደሥራ ሲገቡ አዳዲስ የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣ የሀገር ውስጥ ምርትን ለመጨመርና ሌሎች ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎችን እንደሚያስገኙ ጠቁመው፤ በቀጣይም በተለያዩ ዘርፎች ኢንቨስተሮችን ለመሳብ በትኩረት እንደሚሠራ አብራርተዋል፡፡

ክልሉ በርካታ ማዕድናት የሚገኙበት በመሆኑ የተለያዩ አልሚዎች የማዕድን ዘርፉ ላይ ትኩረት አድርገው ይሠራሉ ያሉት ኮሚሽነር አይሻ፤ የኢትዮጵያን የጨው ፍላጎት በዘርፉ በተሰማሩት የክልሉ ባለሀብቶች ለመሸፈን እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በኢንቨስትመንት ዘርፉ በአጠቃላይ ለ18 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር መታቀዱን ገልጸው፤ የተያዘውን ዕቅድ ስኬታማ ለማድረግ ባለሀብቶች ኢንቨስት እንዲያደርጉ የማነቃቃትና ድጋፍ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በጦርነትና በሌሎች ችግሮች ምክንያት ሥራ ያቆሙ ኢንዱስትሪዎችን ወደሥራ ለማስመለስ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ መጀመር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከቱን አስታውቀዋል፡፡

እንደ ኮሚሽነር አይሻ ገለጻ፤ ክልሉ እስካሁን ድረስ ያልታረሰ ሰፊ ለም መሬት ያለው በመሆኑ ያልታረሰውን ለም መሬት ሙሉ በሙሉ ለማልማት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

በክልሉ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ኢንቨስት እንዲያደርጉ በክልሉ ያለው ሀብት ምንድን ነው? በምን ዘርፍ ቢሠራ ያዋጣል? የሚሉትንና ሌሎች ጉዳዮችን በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት የማሳወቅና ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር የማድረግ ሥራ መሠራቱን አስረድተዋል፡፡

ባለሀብቶች ወደክልሉ መጥተው በሆቴልና ቱሪዝም፣ በእርሻ፣ በማኑፋክቸሪንግና በእንስሳት እርባታ ዘርፎች ቢሰማሩ ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ ተለይቷል ያሉት ኮሚሽነሯ፤ የውጭና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደክልሉ መጥተው መዋዕለ ነዋያቸውን እንዲያፈሱ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ክልሉ ከኦፓል ማዕድን ምርት ከሰባት ሚሊዮን ዶላር በላይ ለማግኘት አቅዶ ወደ ሥራ ገብቷል

## •በሩብ ዓመቱ 324ሺ 428 የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል

**ወርቅነሽ ደምሰው**



አዲስ አበባ፦ በ2016 በጀት ዓመት ከኦፓል ማዕድን ምርት ሰባት ሚሊዮን 200 ሺ በላይ የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት መታቀዱን የአማራ ክልል ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡ በሩብ ዓመቱ 324ሺ 428 የአሜሪካን ዶላር ገቢ መገኘቱ ተጠቁሟል፡፡

የአማራ ክልል ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ታምራት ደምሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት 18ሺ 156 ኪሎ ግራም የኦፓል ምርት ለውጭ ገበያ ለመላክ ታቅዶ እየተሠራ ነው። በተያዘው በጀት ዓመት ውስጥ የኦፓል ምርትን ለውጭ ገበያ በመላክ ሰባት ሚሊዮን 200 ሺህ ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ፤ በሩብ ዓመቱ 10ሺህ 959 ኪሎ ግራም የኦፓል ምርት ለውጭ ገበያ በመላክ 324ሺህ 428 ዶላር ገቢ ማግኘት መቻሉን አስታውቀዋል፡፡ ይህም የኦፓል ምርት እሴት የተጨመረበትንና ያልተጨመረበትን የሚያካትት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የኦፓል ምርት በአብዛኛውን በደቡብ ወሎ እና በሰሜን ወሎ ዞኖች የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰው፤ በሁለቱ ዞኖች በሚገኙት ስምንት ወረዳዎች ሰባት ሺህ 430 ሰዎችን በአባልነት ያካተቱ 69 ኢንተርፕራይዞች ተደራጅተው ኦፓል እያመረቱ ለገበያ እንደሚያቀርቡ ገልጸዋል፡፡

በተያዘው በጀት ዓመትም በማዕድን ዘርፉ ለ45ሺህ 143 ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ እየሠራ ሲሆን በሩብ ዓመቱ ለአራትሺህ 149 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል ብለዋል፡፡

ለውጭ ገበያ የሚላከው አብዛኛው የኦፓል ማዕድን ምርት ምንም ዓይነት እሴት ያልተጨመረበት (ፕሮሰስ ያልተደረገ) ነው ያሉት አቶ ታምራት፤ እሴት ተጨምሮበት ለውጭ ገበያ መላክ ቢቻል ተጨማሪ የሥራ ዕድል ሊፈጥር የሚችል እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ማዕድኑ እሴት ሳይጨመርበት እንዳለ መላክ የዘርፉ ትልቅ ችግር መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህን ችግር ለመቅረፍ ማዕድናት ላይ እሴት በመጨመር የውጭ ገበያውን ፍላጎት ሊያረኩ የሚችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች መጠቀም እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል።

እስካሁን ባለው አሠራር ኦፓልም ሆነ ሌሎች ማዕድናት የሚመረቱት በባሕላዊ መንገድ አነስተኛ ቴክኖሎጂን በመጠቀም እንደሆነ ጠቅሰው፤ ማዕድን ሀብቱን በአግባብ አውጥቶ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችሉ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች መጠቀም እንደሚገባ አስታውቀዋል። ክልሉ ከኦፓል በተጨማሪ እንደ ወርቅ፣ አምበር እና ጂብሰም ዓይነት ማዕድናት ለውጭ ገበያ ለመላክ አቅዶ እየሠራ ነው ያሉት አቶ ታምራት፤ እነዚህ የማዕድን ምርቶቹን ወደ ውጭ ገበያ በመላክ የውጭ ምንዛሪ ገቢን ለማግኘት የሚያስችሉ የተለያዩ የመመሪያ፣ የደንብ እና የአሠራር ማሻሻያዎችን እየተደረጉ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በክልሉ እስካሁን 40 የሚደርሱ ማዕድናትን በጥናት ተለይተዋል የሚሉት አቶ ታምራት፤ ዘንድሮ ዓመትም በጥናት ከተለዩት ውስጥ ሲሊከን የተሰኘ ማዕድን መገኘቱን ገልጸዋል፡፡

ይህንን ማዕድን ለማምረት ለሚፈልጉ ሰባት ባለሀብቶች የማምረት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ፤ ለአንድ ባለሀብት ፈቃድ መስጠቱን ይናገራሉ፡፡ ሌሎች ጂብሰም፣ የድንጋይ ከሰል፣ የኖራ ድንጋይ እና የመሳሰሉ የማዕድናትን ዓይነቶችን በክልሉ የሚገኙ ሲሆን፤ እነዚህ ማዕድናት ለልማት ለሚፈልጉ ለባለሀብቶች ፈቃድ እየተሰጠ መሆኑን ተናግረዋል።

# በቡልቡላ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው

**ሳምራዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፦ በቡልቡላ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆኑን የኦሮሚያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ገለጸ።

የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሮ ሰናይት መብሬ ሰሞኑን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በቡልቡላ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ 29 (30%) ባለሀብቶች መሬት ወስደው 34 ፕሮጀክቶችን ለመጀመር በዝግጅት ላይ ናቸው። ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኩ የሚገቡ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ቁጥር ግን ዝቅተኛ ነው፡፡

ይህ ችግር እንደ ክልል ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገርም ያጋጠመ መሆኑን የቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክን እንደማሳያ ጠቅሰዋል።

መንግሥት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ከ60-80 በመቶ ቅድሚያ ሰጥቶ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሮ በመሥራት ላይ የሚገኝ ቢሆንም የባለሀብቶቹ ተሳትፎ የሚፈለገውን ያህል አይደለም ብለዋል፡፡

በአንድ ሀገር ኢንቨስትመንት ላይ ቅድሚያ የሀገሪቱ ዜጎች በስፋት ቢሳተፉበት ይመረጣል ያሉት ሥራ አስፈፃሚዋ፣ መንግሥት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ከ60 እስከ 80 በመቶ ቅድሚያ ሰጥቶ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሮ በመሥራት ላይ የሚገኝ ቢሆንም የእነርሱ ተሳትፎ የሚፈለገውን ያህል ባለመሆኑ የውጭ ሀገር ባለሀብቶችን ያሳተፈ መሆኑን ተናግረዋል።

ነገር ግን አሁንም የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ፋይዳውን ተገንዝበው ለማልማት የሚፈልጉ ከሆነ በሩ ክፍት ነው ብለዋል።

ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በመንግሥትና በባለሀብቶች ተሳትፎ በማልማት ወደ ምርት እንዲገቡ እየሠራ ነው ያሉት ወይዘሮ ሰናይት፤ በአሁኑ ወቅት



ወ/ሮ ሰናይት መብሬ

ፎቶ - እዮብ ተፈራ

የቡልቡላ የተቀናጀ የግብርና ፓርክን በማጠናቀቅ ለባለሀብቶች አስተላልፎ በሙሉ አቅም ወደ ሥራ ለመግባት መዘጋጀቱን ገልጸዋል።

በነቀምቴ ከተማም የተቀናጀ የግብርና ፓርክ ግንባታም የተጀመረ ሲሆን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ ሥራ ይገባል ተብሎ እንደሚጠበቅ አመልክተዋል።

በተጨማሪም በስድስት ከተሞች ማለትም መቂ፣ ሻሸመኔ፣ ዶዶላ፣ ኢተያ፣ ባሌ ሮቤና አለንጪቲ ውስጥ በገጠር የሽግግር ማዕከላት ደረጃ ፓርኮች መገንባታቸውን አብራርተው፣ እነዚህም የቦታ ስፋታቸው ከትላልቅ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ያነሱ ቢሆኑም፣ አንድ ፓርክ ሊያሟላ የሚገባውን ሁሉ አሟልተው የያዙ መሆናቸውንና ከእነዚህ መካከልም የመቂና ሻሸመኔ ፓርኮች ልማት ተጠናቅቆ ባለሀብቶች እየገቡበት ነው ብለዋል።

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ የፓርኮች ልማት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት።ከእነዚህ መካከልም የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘትና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ይገኙበታል።

«የፓርኮች ልማት ከተጀመረ አጭር ጊዜ በመሆኑ የታሰበለት ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት አንችልም» ያሉት ወይዘሮ ሰናይት፤ «ለምሳሌ የቡልቡላ የተቀናጀ ግብርና ፓርክ ከዓመት በፊት ወደ ሥራ መግባት ነበረበት። ነገር ግን የባለሀብቶች በፍጥነት ወደ ሥራ አለመግባት፣ የምግብ ማቀነባበር ዘርፍ ብዙም የተለመደ አለመሆኑ፣ የብድር አቅርቦት እጥረት፣ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ በታቀደው ጊዜ አለመጠናቀቅና በመሰል ችግሮች የታሰበውን ያህል ውጤት አላስገኘም» ብለዋል።

እንደ ወይዘሮ ሰናይት ገለፃ፣ የቡልቡላ የተቀናጀ የግብርና ፓርክ ውስጥ መሬት የወሰዱ ባለሀብቶች በሙሉ ወደ ሥራ ቢገቡ ከ9ሺህ ለሚበልጡ ሰዎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል፣ በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ ሲገባ ደግሞ ለ30ሺህ ዜጎች በቀጥታ የሥራ ዕድል የሚፈጥር ይሆናል።

ፓርኩ ወደ 271 ሄክታር ስፋት ያለው ሲሆን፣ 135 ሄክታሩ የማምረቻ ዞን እንደሆነ ጠቁመዋል።

ኮርፖሬሽኑ ፓርኮችን ከማልማት ጎን ለጎን የምርት ጥራትን ማረጋገጥና መቆጣጠር፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች የተማሩ ሰዎችን መቅጠር እንዲችሉ ሰዎችን የማሰልጠን እና የገበያ ችግር እንዳያጋጥም ትስስር መፍጠርን ከሚመለከታቸው ሴክተሮች ጋር የመሥራት ግዴታ እንዳለበት አንስተዋል።

ዜና

# መገናኛ ብዙኃን ለውጤታማ ሀገራዊ ምክክር

**አዲሱ ገረመው**

ኢትዮጵያ አሁን በደረሰችበት ደረጃ ለገጠሟት ፈተናዎች መሠረታዊ ምክንያቶችን በመለየት ዘላቂ መፍትሔ ማበጀት እንደሚገባት ይነገራል። እንደ ሀገር የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን በዘላቂነት ለመፍታት ተመራጩ ዘዴ ሀገራዊ ምክክርን ተግባራዊ ማድረግ ስለመሆኑም ብዙዎችን አግባብቷል። ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ሁነኛ መሣሪያ በሆነው የሀገራዊ ምክክር ሂደት መገናኛ ብዙኃን ጉልህ ሚና እንዳላቸውም የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

የአሐዱ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ዋና ሥራ አስኪያጅ ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ እንደሚሉት፤ ከ1966ቱ አብዮት ወዲህ ኢትዮጵያ በፖለቲካ ለውጥ የ50 ዓመታት ያህል ጉዞ አድርጋለች። በዚህ የፖለቲካ ለውጥ ውስጥ ብዙ ውጣ ውረዶች በሀገሪቱ ውስጥ ተከስተዋል። የፖለቲካ አስተሳሰብና ፍልስፍናዎች፣ ግጭቶችና ጦርነቶች ተካሂደዋል። በርካቶች ተፈናቅለዋል። ለሕይወት ህልፈትም ተዳርገዋል። ብዙዎችም ተሰደዋል።

ባለፉት 50 ዓመታት የኢትዮጵያ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ለውጦች የተስተዋሉ ነገሮች ቢኖሩም፤ ግጭቶች ሰፊ ቦታ መያዛቸውን የሚጠቅሱት ጋዜጠኛ ጥበቡ፤ ይህ ወቅት በራሱ ሌላ የታሪክ ሽግግር የሚደረግበት ስለሆነ ምክክር ያስፈልጋል ይላሉ። «በእነዚህ ሁሉ ጉዞዎች ውስጥ ምን ያህል ሰው አጥተናል? ምን ያህልስ ሰው ተጎዳ? ምን ያህሉ አዕምሮው ተነካ የሚሉ ጉዳዮች ተጠንተው ከዚህ በኋላስ ምን ይደረግ የሚሉ ጉዳዮች በውይይት መድረክ መፈታት ይኖርባቸዋል» ሲሉ ይናገራሉ። ለዚህ ደግሞ መገናኛ ብዙኃን ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው ያነሳሉ።

ኢትዮጵያ ካለችበት ሁኔታ አንጻር ሀገራዊ ምክክር የሚያስፈልጋት ወቅት ላይ መሆኗን በመግለጽ፤ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ የያዛቸው ሃሳቦች ወደ መሬት እንዲወርዱና ተግባራዊ እንዲደረጉ ምክክር ኮሚሽኑ ብቻ ሳይሆን መገናኛ ብዙኃንም ጠያቂና ተሳታፊ ሆነው በጋራ ሊሠራ እንደሚገባ ይጠቅሳሉ።

ጋዜጠኛ ጥበቡ፤ «ሀገራዊ ምክክሩ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ጉዳይ ነው። ያሳለፍነውን 50 ዓመታት አይተን ወደ ተሻለ ምዕራፍ በመምጣት ሁላችንም ርብርብ ማድረግ ይኖርብናል። በሁሉም ዘርፍ ከምክክር ኮሚሽኑ ጋር አብሮ መቆም ያስፈልጋል። የጤናና፣ የእርሻ ተቋማት፣ ሚኒስትሩ፣ ነጋዴው፣ ወታደሩ፣ ወዛደሩ፣ ተማሪው፣ ፖሊሱና በሌሎች ዘርፎች የተሰማራ በሙሉ በየመሥሪያ ቤቱና በየአካባቢው መወያየት አለበት። ምንድነው ያሳለፍነው? ምን ጥንካሬ አለን? ምን ችግር አለብን? ከችግሮች እንዴት እንውጣ? የሚለው እያንዳንዱን ይመለከተዋል» ሲሉ ያብራራሉ።

መገናኛ ብዙኃን ሀገራዊ የምክክር ጉዳዮችን ከሌላው የአዘጋገብ ስልታቸውና ዕለት ዕለት ከሚሠሩት ሥራ በተለየ መልኩ አጽንኦት ሰጥተው መሥራት እንዳለባቸው ጋዜጠኛ ጥበቡ ይመክራሉ። ሚዲያዎች የምክክር ኮሚሽኑ ሃሳቦች ሲዘገቡ ምን ዓይነት የአዘጋገብ ስልት መያዝ አለብን የሚለውን በጋራ መወያየት እንዳለባቸው፤ የጋራ ማኑዋልና ኤዲቶሪያል ፖሊሲ ማውጣት እንዳለባቸው ያነሳሉ።

እርስበርስ የሚመካከሩበት፣ የሚገናኙበትና ችግሮቻቸውን ነቅሰው የሚያስተካክሉበት አግባብ እንደሚያስፈልጋቸውና የምክክር ኮሚሽኑ ውጤታማ የሚሆንበትን መንገድ የጀርባ አጥንት ሆነው መሥራት እንዳለባቸውም ይጠቅሳሉ። ለዚህም እርሳቸው የሚመሩት ሚዲያ ቁርጠኛ ሆኖ እየሠራ እንዳለ ያመላክታሉ።

የፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አድማሱ ዳምጠው በበኩላቸው፤ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽንና የሚዲያ ሥራ «የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ» መሆናቸውን ያነሳሉ። የሚዲያ ዋና ሥራ ሃሳብ ማመንጨትና በማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ ሃሳቦችን ወደ ሚዲያው ማምጣት ነው። እነዚህ ሃሳቦች የሚያግባቡ፣ የተሻለ ሕይወት የሚፈጠርበትና የትውልድ ቅብብሎሽ የሚደረግበት፤ ችግሮች ካሉም የሚፈቱበትን አግባብ ጠቋሚና መንገድ ማሳያ ነው ይላሉ።

በሀገሪቱ የምክክር ኮሚሽን መቋቋሙ የበለጠ የጋራ የሆኑ ጉዳዮቻችንን ባለን ባህልና እሴት የመወያየት፣ የስክነት፣ ምክንያታዊነትና በጉዳዩ ላይ የመቀራረብና የጋራ የሆኑ ጉዳዮችን ለመያዝ የሚያስችል ነው የሚሉት አቶ አድማሱ፤ መገናኛ ብዙኃን አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመስጠት ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ይገልጻሉ። ይህም ትውልድን የማሻገርና ሀገርን የመገንባት ሚና እንደሆነ ይጠቅሳሉ።

ሀገራዊ ምክክሩ ለመገናኛ ብዙኃን ሥራ ዋነኛ ዓላማና ኃላፊነት ከመሆኑ አንጻር ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት አሳታፊ በሆኑ ፕሮግራሞቹ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ዓላማና ስኬት ከግብ እንዲደርስ ትልቅ ኃላፊነት ወስዶ የተለያዩ የአቀራረብ ስልቶችን ቀርጾ እየሠራ እንዳለ አንስተዋል። የአቀራረብ ስልቶችን (ፎርማቶቹ) ቀጥታ ማኅበረሰቡና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሃሳብ የሚለዋወጡበት የጋራ የሆኑ ሃሳቦች ለሌላው ተደራሽ የሚሆኑበትን የሚያደርግ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ከሀገራዊ ምክክሩ ጋር ተያይዞ ያሉትን መረጃዎች ተደራሽ በማድረግ ሂደት ውስጥ የመገናኛ ብዙኃን ሚናና የተግባቦት ሥራ ጉልህ መሆኑን በመጥቀስ፤ ምንነቱን መረዳትና ለኅብረተሰቡ ማስረዳት እንደሚያስፈልግ፤ ነገን የተሻለ የማድረግ የትውልድ ሥራም ከመገናኛ ብዙኃን የሚጠበቅ ኃላፊነት እንደሆነ ይናገራሉ። ለውጤታማነቱም ምክንያታዊ የሆነ እሳቤን የማስገንዘብ ሥራ ከመገናኛ ብዙኃን ይጠበቃል ይላሉ።

የኦሮሚያ ብሮድካስቲንግ ኔትወርክ ዋና ዳይሬክተር አቶ ግዛቸው ገቢሳ፤ መገናኛ ብዙኃን የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑን አዋጅ ለኅብረተሰቡ ከማሳወቅ ጀምሮ ለተግባራዊነቱ ትልቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ይገልጻሉ። በዚህ ሂደት ለኅብረተሰቡ መረጃ ከመስጠትና ተጨባጭ ሀገራዊ ሁኔታዎችን ከማስረጽ አንጻር መገናኛ ብዙኃን የራሱን ሚና ቢወጣ ሀገራዊ ምክክሩ ውጤታማ እንደሚሆን አቶ ግዛቸው ይናገራሉ።

መገናኛ ብዙኃኑ የሚጋብዛቸው የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችና ልኂቃንን ለመጠየቅ መሠረታዊ ጉዳዮችን ማወቅ ተገቢ እንደሆነ በማንሳት፤ ከዚህ አንጻር ሚዲያዎች ራሳቸውን ዝግጁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ይላሉ። በዚህም እርሳቸው የሚመሩት የኦቢኤን ሚዲያ ለሀገራዊ ምክክሩ ውጤታማነት በ18 የሀገር ውስጥ ቋንቋዎች የኮሚሽኑ የሥራ ሂደት የሚጠይቃቸውን ጉዳዮች ተደራሽ በማድረግ ላይ እንደሆነ ይገልጻሉ። የአጀንዳው ባለቤት ሕዝቡ መሆኑን በማመን ከአዋጁ ጀምሮና የተሳታፊ ልየታዎች ላይ ግንዛቤ ከመፍጠር ጀምሮ ፤ አሳታፊና ግልጽነት በሥርዓቱ ሥራ ላይ እንዲውል ከዜና ዘገባ ጀምሮ እስከ ዘጋቢ ፊልም (ዶክመንተሪ) በርካታ ሥራዎች መከናወናቸውን ነው የገለጹት።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን መምህሩ ተሻገር ሽፈራው (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ መገናኛ ብዙኃን በሀገራዊ ምክክር ሂደቱ ውስጥ የማሳወቅ፣ የማስተማር፣ የማገናኘት፣ የውይይት መድረክ የመስጠትና ትክክለኛ ጥያቄዎችን የመጠየቅ ሚናቸውን ይጫወታሉ።

ሀገራዊ ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆን ጉዳዩን ከመረዳት ተነስተው በማንኛውም አውድ ውስጥ የኮሚሽኑን ሀገራዊ ምክክርና አጠቃላይ ሥራዎች ለመሥራት የተቀመጡ የአካታችነት፣ የግልጽነት፣ የተዓማኒነት፣ የመቻቻል፣ መከባበር፣ የምክንያታዊነትና ሌሎችም መርኆዎችን ተመርኩዘው መሥራት ይጠበቅባ ቸዋል ሲሉ ይመክራሉ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሀገራዊ የጋራ ትርክት-ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን ለማጠናከር ወሳኝ ነው!

የተዛቡ/ከፋፋይ ትርክቶች እንደ ሀገር ላለፉት ስድስት አስርተ ዓመታት ብዙ ዋጋ እስከፍለውናል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን ለስደት፤ በሺዎች የሚቆጠሩትን ለሞትና ለአካል ጉዳተኝነት፤ ሀገርንም እንደ ሀገር ከፍ ላለ አለመረጋጋትና የሰላም እጦት ዳርገውናል።

ትርክት የሚነገሩ የመረጃዎች፣ የእውነታዎች፣ የታሪኮች፣ የአፈ ታሪኮች እና የክስተቶች ድምር ውጤት፤ የእውቀት እና የስሜት አቅምን የሚገነባ የመረጃዎች ፍሰት ኃይል ነው፡፡ ይህንን ኃይል በአሉታዊም ሆነ አዎንታዊ በሆነ መንገድ በመጠቀም ተጠቃሚም፤ ተጎጅም መሆን ይቻላል።

በተለይም እንደኛ ባሉ የረጅም ዘመን የሀገረ መንግሥት ታሪክ ላላቸው፤ የብዙ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መኖሪያ ለሆኑ ሀገራት ሕዝቦች ቀጣይ አብሮነት እያንዳንዷ ትርክት ከፍ ባለ ጥንቃቄ መመርመር፤ ለሀገር ሕልውና ለሕዝቦች አብሮ መኖር ያለውን ፋይዳ በአግባቡ ማጤን ያስፈልጋል።

ለዚህም በዋነኛነት የትርክቶችን ትክክለኝነት መመርመር፤ ከአሁነኛ ተጨባጭ እውነታ ጋር ማስተሳሰር፤ ከሁሉም በላይ ሀገራዊ የጋራ (አሰባሳቢ) ትርክትን መፍጠር የሚችሉበትን አቅም ማጎልበት ወሳኝ ነው። ለዚህ ደግሞ የመንግሥት፣ የምሑራን እና የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት ከፍያለ ነው።

ሀገራዊ የጋራ ትርክት የመፍጠሩ እውነታ እንደ ሀገር ኅብረ-ብሔራዊ አንድነትን ለማጠናከር፣ ቅቡልነት ያለው ዴሞክራሲ ለመገንባት፣ በሕዝቦች መካከል ዘላቂ ወንድማማችነትና እህትማማችነት ለመፍጠር፣ የዜጎችን ክብርና ደህንነት ለማስጠበቅ፣ የሕግ የበላይነትና ፍትሕን ለማረጋገጥ፣ የሀገርን ልማት እና ዕድገት ለማፋጠን ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው፡፡

በርግጥ ከዚህ ቀደም ሲነገሩ የቆዩ ከፋፋይ ትርክቶች እንደ ሀገር ብዙ ዋጋ አስከፍለውል። የግጭትና የመበተን አደጋ ውስጥ ከተውናል። ችግሩ በብዙ መስዋዕትነት ተጠብቃ የቆየችውን ሀገራችንን ሊያሳጣን እንደሚችል ለመገመትም የሚከብድ አይደለም፡፡

ይህንን እንደ ሀገር ከፊታችን የተደቀነውን ስጋት በማስወገድ ሀገራዊ አንድነትን አጠናክሮ ለማስቀጠል አለመግባባቶችን በውይይት መፍታት፣ የፖለቲካ ልዩነቶችን ማቀራረብ እና ለጸብ መንስኤ የሚሆኑ ሃሳቦችን በማስወገድ ዘላቂ ሰላምን የሚያጸኑ ሃሳቦች ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል።

እንደ ሀገር የምንፈልገውን ብልጽግና፣ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ሆነ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማረጋገጥ የሚቻለው ሀገራዊ ትርክትን መገንባት ሲቻል መሆኑን አምኖ መቀበልንና መተግበርን ይጠይቃል፡፡

ሀገራዊ ትርክትን መገንባት ሲቻል የነገሮችን ትስስርና አመጣጥ ማወቅ፣ ለሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ችግሮች የጋራ መፍትሔ ማስቀመጥ፤ ሀገራዊ ዘላቂ ሰላም መፍጠር ከፍ ባለ ብሔራዊ መነቃቃት ልማትን በማፋጠን ወደ ብልጽግና የሚደረገውን ጉዞ ማፋጠን ይቻላል፡፡

በተለይ አሁን ላይ ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉት የሽግግር ፍትሕ እና ሀገራዊ ምክክር የተያዘላቸውን ግብ እንዲያሳኩ በማድረግ የነበሩትን ቁርሾዎች አስወግዶ ሀገራዊ ትርክትንና የተሻለች ኢትዮጵያን መፍጠር የሚቻልበት ዕድል ሰፊ ነው፡፡

የሚያራርቅ ትርክትን አስወግዶ ሀገራዊ ትርክትን ለመገንባት ታሪክን ማወቅ፣ የሚከፋፍሉ ሃሳቦችንና ሁኔታዎችን አለመቀበል፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ስፍራ እንዳያገኙና እንዳያድጉ አምርሮ መታገል ከፖለቲካ ተዋናዮች ከምሑራንና ከማኅበረሰቡ የሚጠበቅ ትልቁ አሁነኛ የቤት ሥራ ነው።

ለሀገራዊ ችግሮች የጋራ መፍትሔ ማስቀመጥ የሚቻለውም ሀገራዊ ትርክትን መገንባት ሲቻል ነው፤ ለዚህ ደግሞ ሁሉም ማኅበረሰብ መነጋገር፣ መከባበር፣ መደማመጥ፣ መግባባት እና አንድ መሆን ይኖርበታል፡፡

ከዚህም ባለፈ የሚፈጠረውን ሀገራዊ ትርክት ማኅበረሰቡ እንዴት ሊቀበለው እንደሚገባ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ ፤ ትውልዱ እውነታውን ተገንዝቦ ተግባራዊ እንዲያደርገው የሚያስችሉ አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዛሬም ነገም፤ ስለባሕር በር መነጋገር አስፈላጊም አስገዳጅም ነው!

**ፒያንኪ ዘኢትዮጵያ**

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከጥቂት ሳምንታት በፊት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ስለቀይ ባሕር ጉዳይ ሰፊ ገለፃ ማቅረባቸው ይታወሳል፡፡ ገለፃውን ተከትሎ ጉዳዩ የበርካታ ወገኖችን ቀልብ ስቧል፡፡ የባሕር በር እና የወደብ ጥያቄ ከሦስት አስርተ ዓመታት በላይ ኢትዮጵያውያንን ሲያነጋግር የቆየ አጀንዳ በመሆኑ፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለፃ ተገቢና ሕዝባዊ ውይይቶችን የሚጋብዝ እንደሆነ በበርካታ ወገኖች ታምኖበታል፡፡ በሌላ በኩል ጉዳዩ ተገቢና ወሳኝ አገራዊ አጀንዳ ቢሆንም፣ ወቅታዊ የሀገሪቱ ችግሮች ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ የሚገልፁ ወገኖችም አልጠፉም፡፡

በቅድሚያ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ተፈጥሯዊ አቀማመጥ፣ የሕዝብ ብዛት፣ ጂኦ-ፖለቲካዊ ሁኔታዎች እንዲሁም ዓለም አቀፍ የውሃ ሕግጋት ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ላይ ያላት ጥያቄ ተገቢና ሕጋዊ እንዲሆን ዋስትና ይሰጣሉ፡፡ ኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ኃይል እንደነበረች ታሪክ የሚያውቀው ሐቅ ነው፤ ተፈጥሯዊ አቀማመጧ ለቀይ ባሕር ቅርብ ነው፤ ሀገሪቱ የምትገኝበት የአፍሪካ ቀንድ ጂኦ-ፖለቲካዊ ነባራዊ ሁኔታዎች (ፀጥታና ደህንነት፣ ንግድ፣ የኃያላን አገራት ፉክክር...) የኢትዮጵያን ንቁ ተሳትፎና ክትትል ይፈልጋሉ፤ ከ120 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያላት አገር የባሕር በር አልባ (Land-locked) የመሆኗ መራራ ሐቅ አስደንጋጭና አንገት የሚያስደፋ ነው፡፡

ታዲያ እነዚህ የሚያስቆጩና የሚያስደነግጡ ሐቆች ስለቀይ ባሕር ለማውራት ጊዜ የመምረጥ የቅንጦት እድል ይሰጣሉ? ለመሆኑ ስለቀይ ባሕር ለማውራት ትክክለኛው ጊዜ መቼ ነው? በቀይ ባሕር አካባቢ ያሉ ቀጣናዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ሰፊ የቆዳ ስፋት፣ ትልቅ የሕዝብ ቁጥር፣ ከባሕሩ ጋር ልዩ ታሪካዊና ቅርብ ትስስር ያላትን ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን፣ ‹ትንንሽ› እና ከባሕሩ በብዙ ርቀት ላይ የሚገኙ ሀገራትን ትኩረት በእጅጉ የሚስቡ ናቸው። ከቀይ ባሕር ርቀው የሚገኙ ሀገራት ሁልጊዜም ስለቀይ ባሕር እያሰቡና እያወሩ፣ በቀይ ባሕር ላይ ያለችው ኢትዮጵያ «ስለቀይ ባሕር ለማውራት አሁን ትክክኛለው ጊዜ አይደለም» ማለት አይገባትም፡፡

በእርግጥ በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በርካታ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች እንዳሉ አይካድም፡፡ «ችግር ስላለ ስለሌላ ችግር መወራትና መታሰብ የለበትም» ማለት ግን ተገቢ አይደለም፡፡ ምናልባትም የቀይ ባሕር ጉዳይ ለብዙዎቹ ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮች መፍትሔ የሚሰጥ ዐቢይ ጉዳይ ሊሆን ይችላል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በገለፃቸው፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በዚህ ጉዳይ ላይ መክሮና ዘክሮ፣ ከስሜት ነፃ በሆነ መንገድ አስልቶ ለልጆቹ መልካም ነገር ማስቀመጥ እንዳለበትና አጀንዳው ከፓርቲ ጋር ግንኙነት የሌለው የሀገርና የሕዝብ ብሔራዊ ጥቅም ጉዳይ እንደሆነ በአፅንዖት አስገንዝበዋል። «... ኢትዮጵያ በውሃ የተከበበች ደሴት፣ ነገር ግን ውሃ የሚጠማት ሀገር ናት፡፡ የእኛ ሀገር በሙሉ ዙሪያው ውሃ ነው፤ ግን ውሃ ጥማት አለብን ... በቀይ ባሕር ጉዳይ የማንወያይ ከሆነ ስለስንዴም ሆነ ስለአረንጓዴ ልማት መነጋገር ማቆም አለብን... የቀይ ባሕር ጉዳይ በደንብ ንግግር ያስፈልገዋል፡፡ ቢሆንም ጉዳዩን አንናገረውም፣ አናነሳውም፣ ‹ለግጭት... ነው› ይባላል፤ ግን እንደዚያ አይደለም፤ እኛ ግጭት አንፈልግም...» ብለዋል፡፡

አዎ፣ የቀይ ባሕር ጉዳይ ያልተቋረጠ ንግግርና ድርድር ይፈልጋል፡፡ እኛ ብንሸሸውም እሱ ይከተለናል፡፡ «አጀንዳው ግጭት ይቀሰቅሳል፣ ወዳጆቻችንንና ጎረቤቶቻችንን ያስቀይማል...» ተብሎ የሚታለፍ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ላይ ያላት ጥያቄ የስግብግብነት አልያም ወዳጅን የሚያስከፋ ሳይሆን ፍትሐዊ ተጠቃሚነትንና ዘላቂ ወዳጅነትን የሚያፀና ነው፡፡ በፍትሐዊ ጥያቄ የሚያኮርፍና ለግጭት የሚጋበዝ ወዳጅና ጎረቤት ካለ፣ ወዳጅነቱና ጉርብትናው ከአንጀት ሳይሆን ከአንገት ነበር ማለት ነው፡፡

ይህ ዓይነቱ ወዳጅነት ደግሞ በቀይ ባሕር ብቻም ሳይሆን በሌላ ፍትሐዊ ጥያቄ በሌላ ጊዜም ቢሆን ጭምብሉን አውልቆ መታየቱ አይቀርም፡፡ ኢትዮጵያ የዓባይን ውሃ ሳትጠቀም ከዚህ በላይ መቆየት እንደማትችል በዓባይ ግድብ ግንባታ እንዳሳየች ሁሉ፣ ከቀይ ባሕርም ተገልላ መቀጠል አትችልም። በተለይ የመጪው ጊዜ ነባራዊ ሁኔታዎች ይህን የሚፈቅዱ አይደሉም፡፡

በቀይ ባሕር ላይ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ለኢትዮጵያ ያላቸውን አንድምታ ታሳቢ ያደረጉ ፖሊሲዎችና አሠራሮች ያስፈልጋሉ (እነዚህ አሠራሮች ከብሔራዊ ጥቅም ባሻገር፣ የሕዝቦችን ታሪካዊ ወንድማማችነትና አብሮነት ከግምት ውስጥ ያስገቡ ሊሆኑ ይገባል፤ ኢትዮጵያ ደግሞ ይህን በማድረግ የምትታማ አገር አይደለችም)፡፡ ኢትዮጵያ ከቀይ ባሕር የተነጠለች ሀገር እንድትሆን ያደረጉ አካሄዶች ከዚህ በላይ እንዲቀጥሉ መፍቀድ አይገባም፡፡ ሀገሪቱ ወደ ቀይ ባሕር እንዳትጠጋ የሚሸረቡ ሴራዎችን በጥንቃቄ መመልከትና መመከት ያስፈልጋል፡፡

ኢትዮጵያን ታሳቢ ያላደረጉ በአፍሪካ ቀንድ እና በቀይ ባሕር አካባቢ የሚፈጠሩ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አደረጃጀቶች ውጤታማ እንደማይሆኑ ማስገንዘብና ኢትዮጵያም የእነዚህ አደረጃጀቶች አባል እንድትሆን ጠንክሮ መታገል ይገባል፡፡ ኢትዮጵያን ያላሳተፈ «የቀይ ባሕር ፎረም»፣ «በቀይ ባሕር እና በኤደን ባሕረ ሰላጤ የሚዋሰኑ የዓረብ እና የአፍሪካ መንግሥታትን ትብብርና ቅንጅት የማሻሻል ዓላማ አለኝ» ቢል፣ ትርፉ ትዝብት ብቻ ነው፡፡

ግብፅና ሱዳን አብዛኛው ውሃው ከኢትዮጵያ የሚመነጨውን ዓባይን «የሕልውናችን መሠረት ነው» ካሉ፣ ከቀይ ባሕር ጋር ጥብቅ ታሪካዊና ጂኦ-ፖለቲካዊ ትስስር ያላት ኢትዮጵያም «ቀይ ባሕር ሕልውናዬ ነው» የማለት ሙሉ መብት አላት፡፡ ከቀይ ባሕር ተጠቃሚ ለመሆን ከኢትዮጵያ የተሻለ ታሪካዊ፣ ጂኦ-ፖለቲካዊና ሕጋዊ ጥያቄ የማቅረብ ትክክለኛ መብት ያለው አገር ማን ነው?!

ትናንት ስለቀይ ባሕር እየተነጋገርን ከነበረ ትክክል ነበርን፤ ዛሬ ስለቀይ ባሕር እያወራን ከሆነ ትክክል ነን፤ ነገም ስለቀይ ባሕር የምናወራ ከሆነ ትክክል እንሆናለን፡፡ ትናንትም፣ ነገም፣ ዛሬም፣ ሁልጊዜም ስለቀይ ባሕር ለማውራት ትክክለኛ ጊዜዎች ናቸው። በአጭሩ፣ «ስለቀይ ባሕር ለማውራት ትክክለኛው ጊዜ መቼ ነው?» ለሚለው ጥያቄ ትክክለኛውና ተገቢው መልስ «ሁልጊዜም!» ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን የቀይ ባሕርን ጉዳይ በበላይነት መምራትና ለዓለም ሀገራት ምሳሌ መሆን ሲገባን፣ ቀይ ባሕር ከእጃችን አፈትልኮ የወጣበት አጋጣሚ ታሪካዊ ስህተትና ውርደት መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። ስለቀይ ባሕር ማሰብና መወያየት ይህን ታሪካዊ ስህተት የማረም የረጅሙ ጉዞ መጀመሪያ እርምጃ እንደሆነ መረዳት ይገባል፡፡

ታዲያ በዚህ ረጅም ጉዞ ውስጥ ዋናውና አስፈላጊው ነጥብ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ የተናገሩት ነው ... ትልቅ የጦር ኃይል አለኝ ተብሎ በስሜት ተገፋፍቶ ጉዳዩን በኃይል አስፈፅመዋለሁ ማለት ተገቢ አይደለም፤ የኃይል አማራጭ ተገቢ አይደለም ተብሎ ደግሞ እውነታውን መደበቅና ስለጉዳዩ አለመነጋገር ትክክል አይደለም፡፡ መወያየት፣ መነጋገር፣ መደራደር፣ ሰጥቶ መቀበል፣ በጋራ መጠቀም፣ አብሮ ማደግ፣ ዘላቂ ሰላምና እድገትን እውን ማድረግ! የኢትዮጵያ ፍላጎትም ሆነ ተገቢው መንገድ ይህ ብቻ ነው! **ዛሬም ነገም በሰከነ መንፈስ ስለቀይ ባሕር እናውራ፣ እንነጋገር!**

ፖስቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# የጋራ ትርክት ለጋራ ሀገር !

**ባለፉት ዓመታት አንዳንድ ፖለቲከኞች ለራሳቸው እንዲመች ታሪክ መፃፍ አሊያም ለተከታዮቻቸው የተዛነፉ እና ከእውነት የራቁ ሀሳቦችን ሲሰብኩና ሲያስተምሩ ነበር፡፡ ይህም የሀገሪቱን ዜጎች አብሮ የመኖር እሴት እየሸረሸረ አልፎም ለግጭት ሲዳርግ ቆይቷል**

**ታሪኩ ዘለቀ**

ሀገራት እንደየመልክዓ ምድራዊ አቀማመጣቸው፣ እንደተፈጥሯዊ ፀጋቸው፣ እንደትላንት ታሪካቸውና እንደ ኅብረ ብሔራዊነታቸው የየራሳቸው ብሔራዊ ትርክት አላቸው፡፡ የሁሉም ሀገር ምሥረታ ጥንስስ ከትርክት ይጀምራል፡፡ ሀገር በትርክት ይገነባል። በሀገር ታሪክ ውስጥ የነበሩ የተለያዩ የታሪክ ነገረ መንገዶች/ትርክቶች ከአሉታዊዎቹ ይልቅ አዎንታዊዎቹን፣ ከሚያጋጩት ይልቅ የሚያቀራርቡትን መምረጥ ለሀገር መንግሥት ግንባታ ሂደቱ ትልቅ ሚና አላቸው፡፡

ኢትዮጵያ ለብዙ ሺህ ዓመታት የሀገረ መንግሥት ግንባታ ታሪክ ካላቸው ሀገራት መካከል ትጠቀሳለች፡፡ በእነዚህ ዘመናት ውስጥም ሕዝቦቿዋ አንድ የሚያደርጉ በርካታ ታሪኮች አልፈዋል፡፡ ከዚህ የተነሳም ከሚለያዩን ይልቅ አንድ የሚያደርጉን በርካታ ታሪኮች አሉን፡፡ ይሁንና የግል ጥቅመኞች አንድ የሚያደርጉንን ታሪኮች ከማጉላት ይልቅ ነጠላ ታሪኮችን በመምዘዝ፣ አሉታዊውን ብቻ በማጉላትና የበዳይና ተበዳይ ትርክቶችን በመፍጠር በሕዝቦች መካከል ልዩነቶች እንዲሰፉ፣ አለመተማመንን እንዲነግስ ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ አሁንም እየሠሩ ነው።

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በብልፅግና አመራሮች ሥልጠና ላይ ጠለቅ ያለ ትንተና አቅርበዋል። እንደ እሳቸው ከሆነ፣ አወንታዊ መስተጋብር ቤተሰብን፣ ሰፈርን፣ ሀገርን፣ አህጉርን ወደ ብልፅግና ይወስዳል፡፡ በተቃራኒው አሉታዊ መስተጋብሮች ዜጎች ሁሉንም ነገር በጥርጣሬ እንዲመለከቱ፣ ግራ እንዲጋቡ፣ ያደርጋል። ይህም እየሰፋ ሲሄድ ጭቅጭቅ፣ አለመግባባት፣ አለመደማመጥ፣ ተፈጥሮ ግጭትና ቀውስ ይፈጠራል፡፡

ለዚህ ዋንኛ ምክንያት ሁሉ ነገር የትርክት ውጤት በመሆኑ ነው፡፡ ትርክት የሁሉ ነገር መነሾ ነው፡፡ ውድም፣ ርካሽም፤ የሚወደድም፣ የሚጠላም በትርክት ነው፡፡ ትርክት ወደ ቀናው ወይም ወደ አልቀናው መስተጋብር/መከፋፈፍ እንደሚወስደን ትኩረት ሰጥተው ተናግረዋል። በእርግጥ ሁሉ ነገር የትርክት ውጤት ነው። ጠንካራ የጋራ ሀገራዊ ትርክቶችን መፍጠር የቻሉ ሀገራት በብዙ ተጠቃሚ ሲሆኑ ሀገራቸውን በዓለም አደባባይ ታላቅ ሲያደርጉ ተመልክተናል። በተቃራኒው የሚለያይ/ከፋፋይ ትርክቶች የበዛባቸው ሀገራት ብሔራዊ አንድነታቸው ሳይቀር አደጋ ውስጥ ወድቆ ለማየት ችለናል።

እኛ ኢትዮጵያውያንም ፖለቲከኞች በወለዷቸው መገፋፋት የበዳይና ተበዳይ ንዑስ ትርክት በፈጠረው ቂም ቋጠሮ በብዙ ለመከፋፋል ተገደናል፡፡ በቀደመው ዘመን በነበራት አንድነት በጀግንነት ያስቀለመችው፣ በሥልጣኔ ያሸበረቀ ታሪኳ በግጭቶችና በረሃብ ታሪኮች እንዲጠለሽም ሆኗል። በተለያዩ ወቅቶች ሥልጣን ላይ በነበሩና ለሥልጣን በታገሉ አካላት መካከል በነበረ እሰጣገባ ምክንያት ሀገሪቱ በተለያየ የተቃርኖ ጎራ በተመደቡ የተለያዩ ኃይሎች ስር ውላለች።

እነዚህ ኃይሎች በራሳቸው የታሪክ አረዳድ፣ የየራሳቸውን ንዑስ ትርክትም ፈጥረዋል። ይህም የጨቋኝ ተጨቋኝ ንዑስ ትርክትን ከመፍጠር ባለፈ የጋራ ታሪክ የለንም እስከሚል የተዛባ አረዳድ ድረስ ተጉዟል።

ይህም በኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥትና ብሔረ መንግሥት መካከል የተሻለ ትርክት እንዳይፈጠር አድርጓል፡፡ ከዚህም ባለፈ ጠንካራ የጋራ ኢኮኖሚ መገንባት እንዳይቻል ተግዳሮት ሆኗል፣ በሀገሪቱ ያሉ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባሕል የኢትዮጵያዊነት መገለጫ መሆናቸውን አውቆ በባሕልና እሴት የሚያስተሳስር ጠንካራ ተቋም መገንባት ሳይቻል ቀርቷል፡፡

ታሪክን በታሪክነቱ ከመረዳት ይልቅ ታሪክን የግጭት መንስኤ ቂም መወጣጫ አድርገን የምንወስድ አዝማሚያም ሌላው የጋራ ትርክት ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት እየተፈታተነው የሚገኝ ሀገራዊ ችግር ነው፡፡ ታሪክ መማሪያ ነው። ከእኛ በፊት የሆነው ታሪክ ለዚህ ትውልድ ዛሬዎች ሆነ ነገዎች የተሻሻሉ መሆን የመማሪያ ምጣድ ከመሆን ያለፈ ፋይዳ የላቸውም።

በርግጥ ወቅቱ የራሳቸውን ጥቅም ታሳቢ ያደረጉ የሐሰት እና የፈጠራ ትርክቶች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ግለሰቦች የበዙበት ነው። ይህ ደግሞ እንደ ሀገር የጋራ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትርክቶችን ለመፍጠር ለሚደረገው ጥረት ፈተና መሆናቸው የማይቀር ነው፡፡ በተለይም የሐሰት ትርክቶች እያሳደሩት ያለው ጫና እየከበደ መምጣቱ የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣው ጽንፍ የረገጠ ብሔርተኝነት ለችግሩ መስፋፋት ላቅ ያለውን ሚና ተጫውቷል። ሀገር ከመገንባት ይልቅ የማፍረስ አቅም ሆኗል። ይህም በሀገሪቱ ዘመናት ያስቆጠረውን አብሮ የመኖር ጠንካራ ባሕል እየሸረሸረው ይገኛል ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) እንዳሉትም፣ ትርክት ወደቀናው ወይም ወዳልቀናው ሊወስደን ይችላል፡፡ አሁን ላይ እያደገ የመጣው ብሔረሰባዊ ብሔርተኝነት፤ ‹‹የኔ ብቻ ጥሩ›› ትርክት ሀገር ከማፍረስ ውጭ አያሸንፍም። የታሪክ መዛግብት እንደሚያመለክቱት የትም ሀገር አሸንፎ አያውቅም፣ በእኛም ሀገር አያሸንፍም። ንዑሳን ትርክቶች ውጤታቸው ግጭት ነው። የጥፋት ስምሪታቸውም ጥላቻ ዘርቶ ዜጎች በጥርጣሬ እየተያዩ አብሮ የመኖር ባሕላቸው እንዲጠፋ ማድረግ ነው። በንዑሳን ትርክቶች የሚፈጠሩ መስተጋብሮች ጥላቻን እንጂ ፍቅርን አይሰብኩም። መከፋፈልን እንጂ አንድነትን አያሰርፁም፡፡

ይህም በዜጎች መካከል ጥላቻን ጠንስሶ በበላይና በበታች መርዝ ትርክት ጠምቆ ሀገርን በግጭት አቅል ያስታል፡፡ ቂምና በቀል ውስጥ ሆነን የምንቀሳቀስ ከሆነ አዙሪቱ ይቀጥላል፣ መደማማቱ ይብሳል፤ መበቃቀሉ ይጠነክራል። ስለዚህ ይህ የሆነ ቦታና ቀን መቆም እንዲችል እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቆም ብሎ ማሰብ ያለበት አሁን ነው። ባለፉት ዓመታት አንዳንድ ፖለቲከኞች ለራሳቸው እንዲመች ታሪክ መፃፍ አሊያም ለተከታዮቻቸው የተዛነፉ እና ከእውነት የራቁ ሀሳቦችን ሲሰብኩና ሲያስተምሩ ነበር፡፡ ይህም የሀገሪቱን ዜጎች አብሮ የመኖር እሴት እየሸረሸረ አልፎም ለግጭት ሲዳርግ ቆይቷል፡፡

ተለዋዋጭ የሆነው የሀገሪቱ የኔ የበላይ ያንተ የበታች የሚል የተሳሳተ እይታን ቀርጾ ለዓመታት ተጉዟል፡፡ በዚህም ሀገራዊ የፖለቲካ ባሕሉም የጋራ የሚባል ማንነትና ወደ አንድ የሚያስጠጋ ኅብራዊነትን መፍጠር ሳይችል ቀርቷል፡፡ አለፍም ሲል የፖለቲካ አቋም ልዩነት ለግጭት መንስዔ መሆን ቋሚ መገለጫችን ሆኗል፡፡ በአንድ ወቅት አሜን ተፈሪ የተባለ ሰው በዚህ ጉዳይ ላይ እንደፃፈው፣ የሐሳብ ልዩነቶች በርዕዮተ ዓለም ጎራ ከጫፍ እና ከጫፍ ሆነን ለመጓተት እና ለመዘላለፍ ሲዳርገን አይተናል። የፖለቲካ አቋም ልዩነት ደም ሲያፋስስ ተመልክተናል፡፡ የሐሳብ ልዩነት፤ የልዩነት ጎራ ፈጥሮ፤ የርዕዮተ ዓለም ባንዲራ አስይዞ፤ ይህ ‹‹ወገን›› ያኛው ‹‹ጠላት›› ነው በሚል አስፈርጆ፤ በባላንጣነት ሲያሰላልፈን ቆይቷል፡፡

ይሁንና የሐሳብ ልዩነት፤ የግድ-ሁልጊዜ የግጭት መንስዔ አይሆንም፡፡ የሐሳብ ልዩነት፤ በአንድ መድረክ ተቀምጦ ከመወያየት አያግድም። ሰዎች የተለየ ሐሳብን ይጠሉ ይሆናል እንጂ ሐሳቦች ሰዎችን አይጠሉም። እንዲያውም ሐሳቦች ጥራት እና ብቃት የሚያገኙት፤ የሕግ እና የቋሚ እውነት ማዕረግ የሚቀዳጁት በተቃራኒ ድጋፍ ሐሳብ ነው፡፡

ወጥ የሆነ የፖለቲካ ባሕል ባለመኖሩ ደግሞ ዴሞክራሲን ለመገንባት በሚደረገው ጉዞ ላይ ብዙ እንቅፋት ፈጥሯል፡፡ የአንድ ሀገርና ለአንድ ሀገር የሚተጉ ዜጎችን አንደኛው የሥልጣን ባለቤት ሌላኛው የችግር ባለቤት ሆነው የጎሪጥ እንዲተያዩ አድርጓል፡፡ ይህም በመሆኑ የጋራ የሆነ ፖለቲካ፣ የጋራ የሆነ ማንነት መፍጠር አልቻልንም፡፡ በዚህ ምክንያት ጠንካራ ኢትዮጵያዊ የሆነ የጋራ ማንነት መገንባት አልተቻለም፡፡ የፖለቲካ ባሕላችን የጋራ ማንነታችን ጋር መያያዝ መቻል አለበት፡፡ የኔ ነው የምንለው የኢትዮጵያዊነት ማንነት መኖር መቻል አለበት፡፡ ይህ ሲሆን የተሻለ ትርክት መፍጠር ይቻላል፡፡

የነገዋን ኢትዮጵያን ለመገንባት ያለፉ ታሪካዊ ገጠመኞቻችንን ልንጠቀምባቸው እንደሚገባ ሁላችንንም ያስማማናል፡፡ አሁንም ከመነሻው የት እንደምንደርስ አውቀን መንገድ መጀመር ያስፈልጋል፡፡ ሀገራችንን ወዴት እንደምንወስድ አውቀን በጋራ ተወያይተን በጋራ መወሰን አለብን። ቢያንስ አብዛኛው የሀገሬው ዜጋ የሚያምንበትን መንገድ መከተል አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን የሚወስዱት ወዴት ነው? ትውልዳቸውን መቅረፅ የሚፈልጉት እንዴት ነው? የሚሉትንና መሰል ጥያቄዎች ተለይተው ምላሻቸው መታወቅ አለበት፡፡ ይህ ከታወቀ ያሳለፍናቸውን ታሪካዊ ገጠመኞቻችንን ግብዓት በማድረግ ጠንካራ ብሔራዊ ትርክት ማበጀት እንችላለን፡፡ ብሔራዊ ትርክት መገንባት ሀገረ መንግሥቱን በማፅናት ሰላሟ የተጠበቀ ሀገርን መፍጠር ነው፡፡ ለዚህም በልዩነት ዋልታ ረገጥ ሆኖ ከመቆም ይልቅ ብሔራዊ ማንነትን መቅረፅ ላይ መሥራት ለዘላቂ ኅብረ ብሔራዊነት መጠናከር ሚናው የጎላ ነው፡፡

ታላላቅ ሀገራዊ ትርክት በአብሮነት ጥላ ስር የተሰየመ፣ በአንድነት ሰንሰለት የተገመደ ከዘመን ዘመን የሚሻገር አንድነትን የመፍጠር ጥበብ ነው። በትውልድ መካከል በጊዜ መለዋወጥ ጥሩም መጥፎም ይፃፋል፡፡ ከትላንት መጥፎ ታሪክ ተምሮ ዛሬን ገንብቶ ያለህፀፅ ለትውልድ ለማስተላለፍ ታዲያ ታላላቅ ሀገራዊ ትርክት ያስፈልጋል። ታላላቅ ሀገራዊ ትርክቶች የጥንስሳቸው መነሻ የሚሆነው የጋራ ታሪክ ነው።

የጋራ ታሪክ ለመፍጠር የራሳችንን ብቻ ሳይሆን የሌሎችን መመልከት፣ ከቁምነገር መቁጠር፣ እንደራስ ማሰብና ቁጭ ብሎም በረጋ መንፈስ መወያየት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሳይሆን ከቀረ ለቀጣዩም ትውልድ የበለጡ የመጨቃጨቂያና የመነታረኪያ ብሎም የመጋጫ መንስኤዎችን አስቀምጠን እንዳለፍን ይቆጠራል፡፡

በተለያዩ ጊዜያት ሲመጡና ሲሄዱ የነበሩ መንግሥታት የሄዱበት የየራሳቸው መንገድ ጠንካራ ሀገራዊ የጋራ ትርክት መፍጠር አላስቻለም። ይህም ሀገሪቱ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋቷን እንድታጣ አድርጓታል። እንደ ሀገር ከዚህ ችግር ለመውጣት ፣ ሀገርን በጠንካራ የጋራ ሀገራዊ ትርክት ማነፅ ነው።

ኢትዮጵያ ወደ ተሻለ ጎዳና እንድታመራ ሁሉም ልዩነቱን ወደጎን በመተው በጋራ እሴቶች ላይ ማተኮር ይገባል፡፡ ዋልታ በረገጠ ሀሳብ የሚፈጠሩ ንዑሳን ትርክቶች የተመሰቃቀለ የፖለቲካ ገፅታና ደህንነቱ ያልተጠበቀ ሀገርን ያወርሳሉ፡፡ በታላላቅ ሀገራዊ ትርክት የሚፈጠሩ መስተጋብሮች ግን ሀገርን ወደ እድገት ጎዳና ይወስዳሉ፡፡

ኢትዮጵያውያን አያሌ ዘመናትን የተሻገረ የጋራ ታሪክና የጋራ ዕሴት ቢኖረንም የጋራ ጉዳዮቻችንን በጥቂት ፖለቲከኞች አጀንዳ ተቀይሮ ቆይቷል። ዛሬ ላይ ለአዲሱ ትውልድ የጋራ ትርክትን ማውረስ ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው፡፡ የጋራ ትርክትን በመፍጠር ሂደት ትምህርት ላይ ትኩረት በማድረግ ትውልድ ላይ መሥራት አለበት፡፡ እነዚህ የጋራ ትርክቶቻችን በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ተካተው ትውልዱ እንዲማራቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ደግሞ ፖለቲከኞች፣ ምሑራን፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የሀይማኖት አባቶች ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# ‹‹ሀገራዊ ምክክሩ የትኛውንም ፖለቲካዊ ችግሮች ለመፍታት የምንጠቀምበት ሂደት ነው››

*የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር*
*አምባሳደር መሐሙድ ድሪር*

**እፀገነት አክሊሉ**

በኢትዮጵያ ልሂቃን መካከል በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መግባባት አለመኖሩ እንዲሁም በመካከላቸው ያለው አለመተማመን እና ጥርጣሬ ዴሞክራሲያዊ የሽግግር ሂደቱን ፈታኝ አድርጎት ቆይቷል። በዚህም ምክንያት እንደሀገር ለዓመታት የተከማቸውን የፖለቲካ ችግር በውይይት እና በብሔራዊ መግባባት እንዲፈታ ብዙዎች ሲወተውቱ ቆይተዋል።

በሀገሪቱ የተለያየ አካባቢዎች የሚስተዋሉት ግጭቶችም፣ ለዓመታት እልባት ባላገኙ ታሪካዊ ክስተቶች እና የፖለቲካ አመለካከት ልዩነቶች የመጡ ስለመሆናቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እነዚህ ክስተቶች እና ልዩነቶች በየጊዜው አፋጣኝ እርምጃ እየተወሰደባቸው ባለመሆኑ፣ አሁን እዚህ ደረጃ ላይ መደረሱን ብዙዎች ይጠቁማሉ።

እንደ ሀገር የሚታዩ ፅንፍ የወጡ የፖለቲካ አመለካከት ልዩነቶችን ለመፍታት እና ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት ሀገራዊ ምክክር ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል የሚስማማበት ነው፡፡ ሀገራዊ ምክክር መካሄድ እንዳለበት ከመስማማት አልፎ ፍሬያማ ተግባራትን የሚጠበቅበት ጉዳይም ነው።

ይህን ተከትሎ በኢትዮጵያ ያለው የፖለቲካ ልዩነት በምርጫ ብቻ የማይፈታ በመሆኑ፣ የተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መግባባት ለመፍጠር ያስችላል የተባለውን የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በአዋጅ አቋቁሞ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ነው።

በአዋጅ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከፖለቲካ ወገንተኝነት፣ ከማንኛውም የመንግሥት ወይም ሌላ አካል ጣልቃ ገብነትና ተፅዕኖ ነፃ የሆነ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው ከመሆኑም በላይ ተጠሪነቱም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደሆነ በአዋጅ በግልጽ ሰፍሯል። በሀገሪቱም መተማመን የሰፈነበት የፖለቲካ ሥርዓት ለመመሥረት ይሠራል ተብሎም ይጠበቃል።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን 11 ኮሚሽነሮቹን በየካቲት 2014 ዓ.ም ከተሾሙለት በኋላ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡ ከእነዚህም ጊዜያት ጀምሮ ከሁሉ በላይ የብሔራዊ መግባባት እንዳይኖሩ አድርገዋል በተባሉና ወደፊትም ልዩነቶችን አስፍተው ወዳልተገባ ችግር ውስጥ ይከታሉ የተባለላቸው ችግሮችን በመለየት በምክክር መፍትሔ የማፈላለግ ተልዕኮን ይዞ ሥራ እንደጀመረ ይነገራል።

የሀገራዊ ምክክር ሂደት ገዢ መርሆች ያሉት ነው፡፡ ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆንና የታለመለትን ዓላማ እንዲያሳካ የብዙ ተግባራት ቅንጅት ወሳኙን ሚና ይጫወታል፡፡ በሂደቱ ያለፉ ሀገራትን ተሞክሮ መነሻ አድርጎ መሥራቱም አዋጭነት ይኖረዋል። በዚህ መሠረት እንደ ሀገር የተሠሩ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በማንኛውም ሀገር የሚካሄድ የሀገራዊ ምክክር ሂደት ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት መርሆች የተገዛ መሆን እንደሚገባውም በግልጽ ከማስቀመጡም በላይ የዘርፉ ባለሙያዎችም የሚሉት ይህንኑ ነው፡፡

በግልፅ ከተቀመጡት የሀገራዊ ምክክር ሂደት መርሆዎች አንዱ አካታችነት ነው፡፡ አካታችነት ሲባል በሀገራዊ ምክክር ሂደት ውስጥ በሁለት ዓይነት መንገድ ሊተገበር ይችላል፡፡ የመጀመሪያው በተለያየ ምክንያት በውሳኔ ሰጪነት ድምፃቸው ሳይሰማ የኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን በሂደቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስቻል ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ አካታችነት የሀሳብ ብዝኃነት እንዲኖር ማድረግና በሀገራዊ ምክክር ሂደት ውስጥ አዳዲስ እና ምናልባትም ከዚህ ቀደም ያልወጡ ሀሳቦች እንዲንፀባረቁ ማስቻል ነው፡፡



ሌላው መርሆ የጋራ ባለቤትነት ነው፡፡ በሀገራዊ ምክክር ሂደት ውስጥ ሁሉም ባለድርሻ አካል በምክክሩ ሂደት ውስጥ የባለቤትነት ስሜት ሊሰማው ይገባል፡፡ በሂደቱም ባለድርሻ አካላት ሂደቱ የተሳካ እንዲሆንና ችግሮች ሲያጋጥሙም የመፍትሔው አካል ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡

በሰብዓዊነትና የሌላውን ችግር ለመረዳት መፍቀድ ከመርሆዎቹ መካከል ትኩረት ሊያገኝ የሚገባው ነው፡፡ በሀገራዊ ምክክር ሂደት ውስጥ አንዱ ሌላውን የሚያዳምጠው ምላሽ ለመስጠት ብቻ ሳይሆን ሌላው ወገን ያለበትን ችግር በመረዳት እና ራስን በዛ አካል ቦታ አስቀምጦ በማየት መሆን ይገባዋል የሚለውን አስታራቂና ይበጃል የሚለውን ሃሳብም ማቅረብ ይኖርበታል።

ከመርሆዎቹ አራተኛው የሚመነጬ የመፍትሔ ሀሳቦች ዘላቂነት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህም ሲባል በሀገራዊ ምክክር ሂደት ውስጥ የሚነሱ የመፍትሔ ሀሳቦች ችግሮችን ለአጭር ጊዜ ብቻ የሚፈቱ ሳይሆኑ ዘላቂነት ያለው መፍትሔ የሚሰጡ ብሎም ዜጎች ለሀገራቸው ችግሮች ለዘለቄታው የሚበጁ የመፍትሔ ሀሳቦችን በማመንጨት ማኅበራዊ ውሎቻቸውን የሚያድሱበት ሂደት ሊሆን ይገባዋል፡፡

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነሩ አምባሳደር መሐሙድ ድሪር የኮሚሽኑ ሥራ ውጤት ሊያመጣ የሚችለው ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ያገባኛል በሚል መንፈስ አብሮ ሲራመድ ነው የሚል እምነት አላቸው፡፡ እኛም በእዚህና መሰል ጉዳዮች ዙሪያ ቆይታን አድርገናል፡፡

**አዲስ ዘመን ፦ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ በእስከ አሁኑ እንቅስቃሴው ምን ደረጃ ላይ ነው ማለት ይቻላል?**

**አምባሳደር መሐሙድ፦** ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ የሚሠራውን የሚሄድበትን መንገድና የሚያልፋቸውን ነገሮች ብሎም ውጤታማ ሥራን ለመሥራት የሚከፈሉ ዋጋዎችን በሙሉ ሕዝቡ ሊያውቀው ሊገነዘበው ይገባል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን በአዋጅ ተቋቁሞ ወደ ሥራ ከገባ 17 ወራት አካባቢ እያለፉት ነው፡፡ በእነዚህ ጊዜያት ደግሞ የተለያዩ ተግባራትን አከናውኗል፣ በተለይም ሀገር ካለችበት ሁኔታ አንጻር የሚጠበቅበት ምን ዓይነት ተግባር ማከናወን ነው? የሚለውን በጥልቀት በማየትና በመገምገም ብዙ ርቀቶችን ለመጓዝ ሙከራን አድርጓል፡፡

አሁን ላይ የቅድመ ዝግጅት ጊዜውን አጠናቆ የዝግጅት ምዕራፉንም በማገባደድ ላይ ይገኛል። ይህም ሲባል በመላው ሀገራችን ምን መሠራት አለበት? ተሳታፊ ሊሆኑ የሚገባቸው እነማን ናቸው? የሚለውን የማየትና የመወሰን ሥራንም አብሮ እየሠራ ነው፡፡

በዚህም መሠረት በምክክር ሂደቱ ተሳታፊዎች የምንላቸው የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ሲሆኑ፣ ሁሉም አካታችና አሳታፊ በሆነ መልኩ ያሳትፋል። ለምሳሌ በራሳቸው የሚተዳደሩበት ዘዬ ያላቸውን የማኅበረሰብ ክፍሎችን፣ አርሶ አደሮችን፣ አርብቶ አደሮችን፣ የንግዱ ማኅበረሰብ፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ መምህራን፣ የግልና የመንግሥት ሠራተኞች የሀገር ሽማግሌዎች እና ታዋቂ ሰዎች እድሮች እንዲሁም በተያየ መልኩ ኅብረተሰቡ የሚያገላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ ሁሉ ድምፃቸው መሰማት እና ችግሮቻቸው መታየት ያለበት፡፡ ሀገራዊ በሆነ ጉዳይ ላይ ያላቸው አስተያየትና ሀሳብ መደመጥም ስላለበት ሁሉም ይካተታተሉ ፡፡

ሌላው በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች በግጭቶች ምክንያት ከቀያቸው የተፈናቀሉ ወገኖችም እንደ ዜጋ ሀሳባቸውና አጀንዳዎቻቸውን መሠረታዊና ሀገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚያቀርቡበት መድረክ ሁሉ የማመቻቸት ሥራው በመሥራት ላይ ነው፡፡

እንደሚታወቀው የሀገራዊ ምክክር ሂደት በራሱ ፈዋሽ ነው፡፡ ሕዝቦች ዜጎች ፊት ለፊት አይን ለዓይን ተያይተው መሠረታዊ በሆኑ ችግሮቻቸው ዙሪያ የሚነጋገሩበት ነው፡፡ ለመሸናነፍ ሳይሆን ለመረዳትና እውነትን አግኝቶ ሰላምን ለማምጣት የሚመክሩበት በመሆኑ፣ ኮሚሽኑም ይህንን ታሳቢ ያደረገ ተግባር በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ከኮሚሽኑ ሥራ በፊት ሀገራችን ላይ በሕዝቦች መካከል መቃቃሮች ሲኖሩ፣ በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ሂደቱ አናሳ የነበረ ከመሆኑም በላይ የመጠፋፋት መንገዶችን በሙሉ ሞክረናቸው አልፈናል፡፡ ችግሮችን በአፈሙዝ የመፍታት ኩነቶች ውስጥ ገብተን በግጭት እና በጦርነት ብዙ ዋጋ ከፍለናል፡፡ በርካታ ዜጎቻችን አልቀውብናል፣ ሕዝቦች ከቀያቸው ተፈናቅለዋል፡፡ መሠረተ ልማቶች ወድመዋል፣ ተኪ የሌለው የሰው ልጆች ሕይወት በጣም አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ጠፍቷል። በመሆኑም አሁን ላይ ሁላችንም ወደሀገራዊ የምክክር ሂደት እንግባ ያለነው ይህ መንገድ እንደማያዋጣ አውቀን ነው፡፡ በሌላ በኩልም የመጣንበት መንገድ ሀገርን የሚያወድም፣ ብዙ የሚያከስር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

የሚገርመው ነገር እኛ ወደዚህ የምክክር መድረክ እንድንመጣ ካደረጉን ነገሮች መካከል፣ አሁን እኛ እያደረግን ያለውን ነገር ሲያደርጉ የነበሩና ከዛም እንደ ሀገር መቀጠል አቅቷቸው የፈራረሱ ብዙ የአፍሪካ ሀገራትን አይተናል። ኢትዮጵያ ደግሞ ይህ ዕጣ እንዲደርሳት የሚፈልግ ዜጋ የለም፣ በመሆኑም ሀገራችንን ከዚህ ችግር ማውጣት፣ ማሻገርና ሀገርን መታደግ የሚቻለው በሀገራዊ ምክክር ብቻ ነው፡፡

አሁን የምክክር ኮሚሽኑ የደረሰበት ደረጃ የተሳታፊዎች ልየታ ላይ ነው፡፡ ይህ ሥራ ደግሞ የኮሚሽኑ ሥራ ሆኖ ሳለ የምንተማመንባቸው የማኅበረሰብ ክፍሎችም ሂደቱ ውስጥ እንዲገቡና እንዲያግዙ ጥረቶች ተደርገዋል። እነዚህ የሚያግዙን አካላት ደግሞ የሲቪክ ማኅበራት ምክር ቤት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥምረት፣ የሀይማኖት ተቋማት ጉባኤ፣ መምህራንና ሌሎችም አብረውን እየሠሩና ሂደቱን በቅርብ እየተከታተሉ እየተሳተፉበትም ነው፡፡ ‹‹ሂደቱ አካታችና አሳታፊ ነው››፣ የምንለውም እነዚህን እውነታዎች በመያዝ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን ፦ እስከ አሁን በሄዳችሁበት ልክ በተለይም አብረዋችሁ ከሚሠሩት አካላት ውጪ ያለው የማኅበረሰብ ክፍል ተሳትፎ እንዲሁም ምክክር ያስፈልገኛል ይጠቅመኛል ብሎ የማመን ደረጃው እንዴት ይለካል?**

**አምባሳደር መሐሙድ፦** ትልቁ የተገነዘብነው ነገር ቢኖር በኅብረተሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ጉጉት መኖሩን ነው፡፡ አንዳንዶች ሲገልጹት እንደውም ይህ ለሀገራችን የመጨረሻው እድል

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ወቅታዊ

## ‹‹ሀገራዊ ምክክሩ የትኛውንም...

**ከገጽ 7 የዞረ**

ነውና እድሉን ማጣት የለብንም መጠቀም አለብን ይላሉ፡፡ ይህም ቢሆን ግን ሀገራችን ቀደምት ብሎም ሰፊ ታሪክና ባሕል ያላት ትልቅ አገር ከመሆኗ የተነሳ የምክክር ኮሚሽን ያሉብንን እፀዎች በሙሉ በአንድ ጀንበር ይቀርፋል ማለት ደግሞ ይከብዳል። ነገር ግን መሠረታዊ የሆኑና አሁን ባለው ፖሊሲ ሕግጋት ልንፈታቸው የማንችላቸው መንግሥት ሊፈታቸው ያልቻላቸውን ችግሮች ለመፍታት ይሠራል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በማኅበረሰቡ መካከል እልፍ ልዩነቶች አሉ፤ ይህ ደግሞ እየዋለ እያደረ በመካከላችን ትልቅ ክፍተት እንዲኖር አድርጓል፡፡ ሀገራዊ ምክክሩም ያስፈለገው ከዚህ ለመውጣት ነው፡፡

ይህ ሀገራዊ ምክክር እንዲሳካ የሕዝቡ ፍላጎት መሆኑን ከሄድንባቸው አካባቢዎች በሙሉ ባየነውና በሰማነው ሃሳብ ለመገንዘብ ችለናል። በእርግጥ በነበረው አለመረጋጋት ምክንያት ወደትግራይ ክልል የሄድነው አሁን በቅርቡ ነው፤ በዛም ቢሆን በሄድንበት ጊዜ ከክልሉ አመራሮች ጋር የመጀመሪያው ንግግር ተፈጥሯል፤ በቀጣይ ደግሞ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል እናሳትፋለን፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን የምክክር ኮሚሽኑን ሥራና ሂደት ሁሉም አምኖበትና በፍቃደኝነት እየተሳተፈበት ስለመሆኑ መናገር ይቻላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ሀገራዊ ምክክሩ በምሥራቅ አፍሪካ እንዲሁም በመላው አፍሪካ ተጠቃሽና ውጤታማ እናደርገዋለን ብላችኋልና ይህ ምን ማለት ነው?**

**አምባሳደር መሐሙድ፡-** ምክክር ኮሚሽኑ እየተጓዘ ያለው ትልቅ ራዕይ ሰንቆ ነው ፤ ምክንያቱም ኢትዮጵያን ከታሪክ አንጻር ብንመለከት የመጣነው የነበሩ በርካታ እድሎችን አጥተን ነው፤ እነዛን እድሎች ያጣንበት ዋናው ምክንያት መመካከር አለመቻላችን ነው፡፡ በተደጋጋሚ በግጭት፣ በጉልበትና በኃይል ችግሮች እንዲፈቱ ተሞክሯል፤ አንዳንድ ምክክር መሰል ሂደቶች ቢኖሩም እንዲከስሙ ሆነዋል። ይህኛው ወይም አሁን በሀገራችን የሚካሄደው ሀገራዊ ምክክር አንደኛ አሳታፊነቱ የተጠበቀ ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍል የሚያካትት ተዓማኒነት ያለውና በሕዝቡም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ ይህ ደግሞ በአፍሪካ ውስጥ ከተካሄዱት የምክክር ሂደቶች ሁሉ ግዙፉ ነው ብንል ማጋነን አይደለም። ምክንያቱም ኢትዮጵያ በሕዝብ ብዛት ከፍተኛ ናት፤ የአገሪቱ ታሪክን ስንመለከት ደግሞ በራሱ ገላጭ ነው ፡፡

ሌላው በአፍሪካ ውስጥ የተካሄዱ አንዳንድ የምክክር ሂደቶች ቁንጽል በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተካሄዱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የኬንያን ብናይ ድረ ምርጫ የተከሰቱ ኩነቶችን ለማብረድና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለማጽናት የተካሄደ ነው፤ በአንጻሩ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደው ምክክር የማይዳስሳቸው አጀንዳዎች የሉም፡፡ በጣም ሰፊ ናቸው፡፡ በነገራችን ላይ እኛ እንደ ምክክር ኮሚሽን አጀንዳው ያ ይሁን ወይም ይሄ ይሁን የምንልበት አግባብ የለም፡፡ ሕጉም አይፈቅድም፤ ነገር ግን እስከ አሁን ከተገነዘብነውና ካየነው በሕዝቡ ዘንድ ያለው ስሜትና የተሳታፊዎች ልየታ በተካሄደባቸው አካባቢዎች ሁሉ በሚደረጉ ስብሰባዎች፤ ምክክር የሚመስሉ ነገሮች ይካሄዳሉና እንደ ግብዓት በሰበሰብነው መረጃም የታዘብናቸው ብዙ ነገሮች አሉ።

ከግጭት አፈታት አንጻር ደግሞ የሩዋንዳው ሂደት በጣም የተሳካና የሰመረ ነው ይባልለታል። እውነት ነው፤ የተሳካ ስለነበር ሀገሪቱን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሂደት ያሸጋገረ ሆኗል፡፡ ነገር ግን ግጭቱ በሁለት ጎሳዎች መካከል የተካሄደ ነበር። እኛ አገር ውስጥስ ችግሮች ያሉት በስንት ጎሳዎች መካከል ነው? ይህንን ቤት ይቁጠረው። በመሆኑም መሠረታዊ የሆኑትን ልዩነቶቻችንን በጥብቅና ሕዝቡ ራሱ በተሳተፈበት አግባብ የሚፈታበት ሂደት ይኖራል ማለት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኮሚሽኑ የውጭ አገር ስኬታማ የምክክር ውጤቶችን እንደ ተሞክሮ መውሰዱ ጥሩ ሆኖ ሳለ፤ ግን ደግሞ እንደ ሀገርም ብዙ የግጭት አፈታት ሂደት ያለን በመሆኑ እሱን ተሞክሮ ለመቀመር የተሄደበት መንገድ ይኖር ይሆን?**

**አምባሳደር መሐሙድ ፡-** በሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የምሥረታ አዋጅ ላይ የተጠቀሰ ጉዳይ ነው። ይህም ማለት የአዋጅ ቁጥር 1265/2014 ሀገር በቀል እውቀትን መጠቀም እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ በመሆኑም እነዚህን በተለይም የግጭት አፈታት፤ የመመካከር እና የመደማመጥ ባሕሎች በሰፊው ሀገራችን ላይ ይታያሉ። ያም ቢሆን የተጠቀምናቸው እስከ አሁን በጣም ውስን በሆኑ ጉዳዮቻችን ላይ ብቻ ነው። በመሆኑም እነዚህን እውቀቶች ወደሀገራዊ ምክክሩ እንዴት ልናመጣቸው እንችላለን? እንዴት እንጠቀምባቸው? የሚለው እየታሰበበት ከመሆኑም በላይ ወደምክክር ሂደቱ ዓውድ ስንገባ የምንተገብረው ይሆናል ብዬ አስባለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንድ ወገኖች የምክክር ሂደት የሚባለው ነገር የመንግሥት የፖለቲካ መጠቀሚያ ነው ይላሉና እንደው እርስዎ በዚህ ላይ ምን አስተያየት አልዎት?**

**አምባሳደር መሐሙድ፡-** ሀገራዊ ምክክር የፖለቲካ መጠቀሚያ ሳይሆን፤ የትኛውንም ፖለቲካዊ ችግሮች ለመፍታትና ለመቅረፍ የምንጠቀምበት ሂደት ነው፡፡ ነገር ግን የመንግሥት የፖለቲካ መጠቀሚያ ነው የሚሉ ወገኖች ሀሳቡ የራሳቸው ስለሆነ መተው የሚሻለው ነው፡፡ ሆኖም ሀገራዊ ምክክሩ የሕዝብ ነው፡፡ የሕዝብ ነው ስንል ደግሞ ሕዝብ በራሱ አንደበት አጀንዳዬን ወደ መንግሥት ያቀርቡልኛል ብሎ የሚያምናቸውን ሰዎች ወክሎ ይልካል፡፡ እነዛ ተወካዮች ደግሞ አጀንዳዎቹን ይዘው በመምጣት ይቀረፃሉ፤ ይህ አጀንዳ ደግሞ ከኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ዜጎች ካሉባቸው ዓለማት በሙሉ የሚላኩ ናቸው፡፡ አጀንዳዎቹ ከተሰበሰቡ በኋላ ምክር ቤቱና አማካሪ ካውንስሉ በመቅረጽ ለሕዝብ ይፋ እንዲሆን ይሆናል፡፡ በዚህም ሕዝቡ ምክክር ኮሚሽኑ ሂደቱን የሚያደርገው በእነዚህ አጀንዳዎች ዙሪያ ነው ሲል ይፋ ያደርጋል፤ ምንም የተደበቀ ነገር አይኖርም ማለት ነው፡፡

አጀንዳው ከሕዝብ የመነጨ፤ እንደገና ለሕዝብ የተላለፈ፤ በዚህ ሂደት ውስጥ ደግሞ የመገናኛ ብዙኃን ተሳትፎ በእጅጉ የሚፈለግና ጠቀሜታውም ላቅ ያለ ነው፡፡ ይህ ከሆነ በኋላ ምክክር ይካሄዳል፤ ምክክሩ ተካሂዶ የሚወጡ ምክረ ሀሳቦች ደግሞ ዝም ብለው የሚቀመጡ ሳይሆኑ፤ መንግሥት እንዲተገብራቸው የሚሰጡ ናቸው፡፡ መንግሥት በቃ ይተግብራቸው ብሎ ደግሞ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ አይበተንም፡፡ ምን ያህሎቹ ተተገበሩ? በምን አግባብ ተስተናገዱ? ብሎ ያያል ይጠይቃል፤ ይከታተላል፡፡ በመሆኑም ሀገራዊ ምክክሩ ይሳካል፤ ከአፍሪካም ቀዳሚ ይሆናል ብለን የምንገልጸው በእነዚህ ምክንያቶች ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የምክክር ኮሚሽኑ ላይ ያለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳትፎ እንዴት ይገለጻል?**

**አምባሳደር መሐሙድ፡-** እስከ አሁን ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በዚህም ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ ይህ ጥረት ግን ወደፊትም ተጠናክሮ የሚቀጥል ነው፤ ምክንያቱም ሁሉንም ያሳተፈ ስንል መንግሥት ሊሰማው የሚፈልገውን የፖለቲካ አስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን መንግሥት ሊሰማው የማይፈልገውንም ሀሳብ ሀገራችን ላይ እስካለ ድረስ፤ እነዚህም አካላት የምክክሩ አካል የማይሆኑበት ሂደት ፈጽሞ አይኖርም፡፡



እስከ አሁን ድረስ ከተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር እየተቀራረብን እንሠራለን፡፡ በሂደቱ ጥርጣሬ ያላቸው አሉ፡፡ ይህም የራሳቸው አቋም በመሆኑ ምንም ማድረግ አይቻልም፡፡ ነገር ግን ከዚህ ጥርጣሬ እንዲወጡ ለማድረግ በእኛ በኩል የማያቋርጡ ጥረቶች ይደረጋሉ። ሆኖም የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን እነዚህ ሰዎች አቋማቸው የተለየ ነው ብሎ የማግለል ፍላጎት የለውም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ምክክር ኮሚሽን አሁን በሥራችሁ ላይ ዋና ተግዳሮት የሆነባችሁ ነገር ምንድነው?**

**አምባሳደር መሐሙድ፡-** በሀገሪቱ ያለው የሰላም መደፍረስ ትልቁ ተግዳሮታችን ነው። በእርግጥ ሀገራዊ ምክክር የሚካሄደው በሰከነና በተረጋጋ ሁኔታ ብቻ አይደለም፤ በአንጻሩ ግጭቶች ባሉበት ቦታ ሁሉ የሚካሄድበት አጋጣሚም አለ። ይህ ከመሆኑም በላይ የግጭት ተዋንያንም መሣሪያቸውን አስቀምጠው ወደ ምክክሩ እንዲገቡና የምክክሩ አካል እንዲሆኑ ይፈለጋል። በሌሎች ሀገሮችም በዚህ መልኩ የተሄደባቸው ሁኔታዎች አሉ ፤ እነዚህንም ተሞክሮዎች ቀምረን በሀገራችን ውስጥ ነፍጥ ያነሱ ወገኖች ወደምክክሩ እንዲመጡ ጥረቶቹ ይቀጥላሉ፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- እዚህ ላይ ግን አምባሳደር በተለይም ጽንፍና ጽንፍ ያሉ ሀሳቦችን ይዘው ነፍጥ ያነገቡ አካላትን ወደ አንድ ማምጣት ለኮሚሽኑ ፈተና አይሆንበትም? እንዴት እንወጣዋለን ብላችሁ ታስባላችሁ?**

**አምባሳደር መሐሙድ፡-** ትልቁ የምክክር ሂደቱ ተግባር ብሔራዊ ሀገራዊ መግባባትን መፍጠር ነው፡፡ ይህንን ሀገራዊ የጋራ መግባባትን ለመፍጠር በግልጽ በጋራ መምከር ችግሮችን በግለሰቦች በቡድኖች ላይ ሳይሆን በችግሮቹ ዙሪያና እነሱን ለመፍታት በጎና ቀናኢ መሆንን ይጠይቃል፡፡ ስለዚህ የሀገራዊ ምክክር ውጤቱ ሀገራዊ የጋራ መግባባትን የጸና የመንግሥት ሥርዓት መገንባትን አዲስ የሆነ ፖለቲካዊ ምዕራፍ ማስጀመር ነው፡፡

እዚህ ላይ ግን በሀገራዊ ምክክሩ ሁሉም ችግሮች ይፈታሉ የሚል እምነት የለንም፡፡ ነገር ግን መሠረታዊ የሆኑ ችግሮች ከተፈቱ በቀጣይነት ሌሎቹም የማይፈቱበት ምክንያት የለም ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ይህ የምክክር ሂደት ውጤታማ ይሆን ዘንድ ከማን ምን ይጠበቃል?**

**አምባሳደር መሐሙድ፡-** ከሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ተሳትፎ ይጠበቃል፡፡ ከአረጀውና ለዘመናት ወደነውጥ ወደግጭትና ነፍጥ ወደማንሳት ሲወስደን ከነበረው አስተሳሰብ ወጥቶ በሰከነና በተረጋጋ ዓውድ ውስጥ ገብቶ ወደምክክሩ መቀላቀል እንዲሁም ይወክለኛል የሚላቸውን ተሳታፊዎች በአግባቡ መምረጥ ይጠበቅበታል፡፡

በሌላ በኩል ተሳታፊዎች ከውስጥና ከውጭ ጫና ራሳቸውን አግለው የማይበገሩ መሆን፤ ከግል ጥቅም ይልቅ ሀገራቸውን የሚያስቡና የሚያስቀድሙ መሆን አለባቸው፡፡ ሀገራቸውን ካለችበት ችግር ለማላቀቅ ሌት ተቀን የሚሠሩ ዜጎች መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ ቁመና ላይ ከታየን ደግሞ የሀገራችንን ችግሮች ለይተን አለመግባባቶቻችንን ለመፍታት እንችላለን የሚል እምነት አለን፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- እስከ አሁን ከመጣችሁበት መንገድ ተነስተው፤ ቢሆን ብለው የሚመኙትን መልዕክት ያስተላልፉ?**

**አምባሳደር መሐሙድ፡-** በውስጥም በውጭም ያለን ኢትዮጵያውያን ይህንን እድል ተጠቅመን ሀገራችንን ከችግሮቿ እንድትላቀቅ ሕቦቿም በእኩልነት በዴሞክራሲና በሰላም እንዲኖሩባት፤ የሰላሙ ትሩፋት ደግሞ ወደልማት አንቀሳቅሶን ሀገር እንድንገነባ የታሪክ ተወቃሽ እንዳንሆን አምላክ ይርዳን!

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ፡፡**

**አምባሳደር መሐሙድ፡-** እኔም አመሰግናለሁ

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ፈጣንና ሙሉ ትግበራ የሚያሻው የነፃ ንግድ ቀጣና አሰራር

**አንተነህ ቸሬ**

ሀገራት የወጪና ገቢ ንግዳቸውን ለማቀላጠፍና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰታቸውን ለማሳደግ ብሎም አጠቃላይ ምጣኔ ሀብታዊ እድገታቸውን ለማሻሻል ከሚተገብሯቸው አሰራሮች መካከል አንዱ ነፃ የንግድ ቀጣናዎችን (Free Trade Zones) ማቋቋም ነው፡፡ ነፃ የንግድ ቀጣና ‹‹ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣና›› (Special Economic Zones) የሚባሉት የንግድና ኢንቨስትመንት መከወኛ ስፍራዎች አካል ሲሆን፣ እሴት የሚጨምሩ የምርት፣ የሎጅስቲክስ፣ የፋይናንስ አቅርቦትና መሰል ተግባራትና አገልግሎቶች የሚከናወኑበት ቦታ ነው፡፡

በዚህ ስፍራ ምርቶችን ከማምረት በተጨማሪ አስመጪና ላኪዎች ዕቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ በማምጣት በቀጣናው ውስጥ የሚያከማቹበት፣ የሚያቀነባብሩበት እንዲሁም መልሰው ለውጭ ገበያዎች የሚያቀርቡበት እንዲሁም ሂደቱን ለማሳለጥ ቀልጣፋ የሆነ የሎጂስቲክስ አገልግሎት የሚቀርብበትም ነው፡፡ የተቀናጁ የፋይናንስና የምክር አገልግሎቶችም ይሰጥበታል፡፡

ነፃ የንግድ ቀጣና ኢንቨስትመንትን የሚጨምር፣ አዳዲስ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር የሚያግዝ፣ ቢሮክራሲያዊ የአሰራር ውጣ ውረዶችን የሚቀንስ አማራጭ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ይህ ቀጣና የንግድ እንቅፋቶች የሌሉበት እንዲሁም ቀረጥና ግብር ያነሰበት የንግድና ኢንቨስትመንት ማሳለጫ አካባቢ እንደሆነም ይገለፃል፡፡ በነፃ የንግድ ቀጣናዎች ውስጥ የሚተገበሩ ሕጋዊ አሰራሮች በሌሎቹ አካባቢዎች ከሚተገበሩት ጋር ሲነፃፀሩ የላሉና አንፃራዊ ነፃነትን የሚያጎናጽፉ ናቸው። እነዚህ አሰራሮች ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረዶችን የሚቀንሱ በመሆናቸው ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ለመሰማራት የሚያደርጉትን ጥረት በአንፃራዊነት ቀላል ያደርጉላቸዋል፡፡

ነፃ የንግድ ቀጣናዎች የሚፈጥሩትን የሥራ እድል፣ ለሀገር በቀል የሎጂስቲክስ ኢንዱስትሪው መስፋፋት የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግርና የባለሙያዎችንና የሠራተኞችን ክህሎት ለማሳደግ እና ለዋጋ ግሽበት መቀነስ የሚኖራቸውን ወሳኝ ሚና፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰትን ለማሳደግ እንዲሁም የወጪና ገቢ ንግድን ለማቀላጠፍ ያላቸውን አበርክቶ በአጠቃላይ ለሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት መሻሻል የሚኖራቸውን ጉልህ ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሀገሮች ነፃ የንግድ ቀጣናዎችን ያቋቁማሉ፣ ያስፋፋሉ፡፡

መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ በዓለም ላይ ከአምስት ሺ በላይ ነፃ የንግድ ቀጣናዎች አሉ። በርካታ ሀገራት ነፃ የንግድ ቀጣናዎች ያሏቸው ሲሆን፣ ለእዚህም የኢትዮጵያ ጎረቤቶች የሆኑት ጅቡቲ፣ ኬንያ፣ ሱዳን ተጠቃሽ ናቸው። ዛሬ በምጣኔ ሀብታቸው የበለፀጉት ሀገራትም ይህን የነፃ ንግድ ቀጣና አሰራር ተግባራዊ አድርገዋል፤ እያደረጉም ይገኛሉ፡፡

ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር እንዲሁም መሬትን ጨምሮ ሌሎች እምቅ ሀብቶች ያላት ኢትዮጵያ ነፃ የንግድ ቀጣናን እስካሁን ድረስ ባለማቋቋሟ ማግኘት የሚገባትን ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅም ማጣቷ ተደጋግሞ ሲገለጽ ቆይቷል። የሀገሪቱን የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ እግር ከወርች አስረው የያዙት አንዳንዶቹ መሰናክሎች ነፃ የንግድ ቀጣናዎች በሚያስገኟቸው ጥቅሞች የሚፈቱ ናቸው፡፡

ስለሆነም ነፃ የንግድ ቀጠና በማቋቋም የሀገሪቱን ተጠቃሚነት ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ ልዩ ልዩ የመሠረተ ልማት አቅርቦትና የሕግ ማዕቀፍ ዝግጅቶች ሲደረጉ ቆይተው፣ የኢትዮጵያን የወጪና ገቢ ንግድ በማቀላጠፍና የኢንቨስትመንት ፍሰቱን በመጨመር ለሀገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ተስፋ የተጣለበት የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና (Dire Dawa Free Trade Zone)፣ ነሐሴ 8 ቀን 2014 ዓ.ም በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተመርቆ ሥራ እንደጀመረ ይታወሳል። በድሬዳዋ የሚገኘውን የኢንዱስትሪ ፓርክና ደረቅ ወደብን ከዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት፣ ከባቡርና ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር በማቀናጀት እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ የባንክና የጉምሩክ አገልግሎቶችን ተደራሽ በማድረግ ወደ አገልግሎት እንዲገባ ለማድረግ የሚያስችሉት ተግባራት ሲከናወኑ ከቆዩ በኋላ ሥራ እንዲጀምር የተደረገው ነፃ የንግድ ቀጠናው፤ ለበርካታ ዓመታት ከነፃ የንግድ ቀጠና አሰራር ርቆ ለኖረው የኢትዮጵያ ንግድና ኢንቨስትመንት ዘርፍ እድገት ትልቅ አበርክቶ እንደሚኖረው ተገልጿል፡፡ ነፃ የንግድ ቀጠናው በመጀመሪያ ምዕራፍ ግንባታው በ150 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን አራት ሺ ሄክታር መሬት የማስፋፊያ ቦታ ተዘጋጅቶለታል፡፡

> **አዋጁ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተመርቷል፡፡ የነፃ የንግድ ቀጣናው በሙሉ አቅሙ ወደ ሥብ መግባት የዋጋ ግሽበትን በመቀነስ፣ የግብርና ግብዓቶችን አቅርቦት በማሳደግ፣ የኢንዱስትሪ ግብዓት ፍላጎትን በማሻሻል፣ የንግድና ሎጂስቲክስ አገልግሎቶችን በማቀላጠፍ ረገድ ለሀገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፣ አዋጁ በፍጥነት ጸድቆ ወደ ሥራ እንዲገባ ጥረት ይደረጋል**

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ፣ ነፃ የንግድ ቀጠናው የሀገሪቱን የንግድ እንቅስቃሴና የሎጂስቲክስ ፍላጎት መጨመርን ታሳቢ አድርጎ የተቋቋመ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና ኢትዮጵያን ለኢንቨስትመንት ምቹ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት አካል ነው›› የሚሉት ዋና ሥራ አስፈፃሚው፣ ነፃ የንግድ ቀጠናው ድሬዳዋንና አካባቢውን የሚያነቃቃ፣ ለነዋሪዎች የሥራ እድል የሚፈጥር እና የወጪና ገቢ ንግድን የሚያሳልጥ ከመሆኑም ባሻገር ማክሮ ኢኮኖሚውን ለማነቃቃት እና በሀገራዊ ምጣኔ ሀብት ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣት የሚያግዝ ግብዓት ሆኖ ያገለግላል፡፡

‹‹ነጻ የንግድ ቀጠናው የውጭ ምንዛሬ እንዲገኝ ከማስቻሉ በተጨማሪ ተኪ ምርቶች እንዲመረቱ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ሀገሪቱ ምርቶችን ከውጭ ለማስገባት የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ በማስቀረት ረገድም ከፍተኛ ሚና ይጫወታል›› ይላሉ። የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽንም በድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠናም ሆነ በሌሎች የኢንዱስትሪ ፓርኮች ለመሰማራት ጥያቄ የሚያቀርቡ ባለሀብቶችን በፍጥነት ለማስተናገድ እየሰራ እንደሚገኝም ይናገራሉ፡፡

አቶ አክሊሉ እንደሚያብራሩት፣ ነፃ የንግድ ቀጣናው የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ለደንበኞች ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶችን አሟልቷል፤ የአሰራር ሥርዓቶችን ዘርግቷል፡፡ የባለሃብት ምልመላ መስፈርትና የአገልግሎት ዋጋ ተመን አዘጋጅቷል፡፡ የተለያዩ ሀገራት በነፃ የንግድ ቀጣና አስተዳደር ዘርፍ ያላቸውን ልምድና ተሞክሮ ተቀምሯል፡፡

በዚህ ረገድ የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች፣ የቱርክና የጅቡቲ ተሞክሮ ተጠንቶ የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና ባለበት ሥነ ምህዳራዊና ፖለቲካዊ አስተዳደር ውስጥ ተወዳዳሪና ተመራጭ እንዲሆን ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው አሰራሮች ተግባራዊ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ ነፃ የንግድ ቀጣናው ለአምራቾች፣ ለአስመጪዎች፣ ለላኪዎችና ለሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች አመቺ እንዲሆን ተደርጎ ከመልማቱ በተጨማሪ ከዋና ዋና የትራንስፖርት መሠረተ ልማት አማራጮች በቅርብ ርቀት ላይ መገኘቱ ተመራጭ ያደርገዋል፡፡

እስካሁን ድረስ የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና ከወጪ ንግድና ከተኪ ምርቶች ምርት ሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ገቢ አስገኝቷል፡፡ ቀጣናው በሚቀጥሉት ወራት በሙሉ አቅሙ ማምረት ሲጀምር ሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴን በማነቃቃት ረገድ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ ነፃ የንግድ ቀጣናው በመሠረተ ልማት አቅርቦት ረገድ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የቴሌኮም አገልግሎት፣ የውሃ አቅርቦት፣ የፍሳሽ ማጣሪያ፣ ለቢሮና ለንግድ የሚሆኑ ሕንፃዎች፣ ለማምረቻና ማከማቻ የሚያገለግሉ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖች፣ መሠረተ ልማቶች የተሟሉለት 48 ሄክታር የለማ መሬት፣ የምርት ማሳያ ቦታዎችን አካትቶ በዓለም አቀፍ ልምድ መሠረት ሥራ እንዲጀምር ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡

የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ካሚል ኢብራሂም በበኩላቸው፣ ነፃ የንግድ ቀጠናው በይፋ ከተመረቀ በኋላ ብዙ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በነፃ ንግድ ቀጠናው ውስጥ ለመሰማራት ፍላጎት እያሳዩ እንደሆነ ይናገራሉ። እንደ አቶ ካሚል ገለፃ፣ ነፃ የንግድ ቀጠናው ከተመረቀ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ወደ ቀጠናው ገብተው በኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይ የሚሰማሩ ድርጅቶችን ለማስተናገድ የሚያስችሉትን ተግባራት ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ ከእነዚህም መካከል መዋቅር የመዘርጋት፣ በዘርፉ ልምድ ካላቸው ሀገራት ተሞክሮ በመቀመር የታሪፍ መመሪያ እና ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የባለሀብቶች መመልመያ መስፈርት እና የውጭ ምንዛሬ አጠቃቀምን ጨምሮ የፋይናንስ መመሪያዎችን የማዘጋጀት ተግባራት ይጠቀሳሉ፡፡

‹‹ነፃ የንግድ ቀጠናው በሌሎች ሀገራት ከሚገኙ ብዙ ነፃ የንግድ ቀጠናዎች ያላነሰ የመሠረተ ልማት አቅርቦት አለው፡፡ በዚህም ምክንያት በቀጠናው ውስጥ ገብተው በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ቁጥር ጨምሯል፡፡ በ2015 የበጀት ዓመት የሕግ ማዕቀፎች ሲዘጋጁና ከተለያዩ ሀገራት ተሞክሮዎች ሲቀመሩ ቆይቷል፡፡ መሠረተ ልማቶችን የማሟላት ሥራዎች ተሰርተዋል›› ይላሉ። ነፃ የንግድ ቀጣናው ከምርት ተግባር በተጨማሪ በንግድና በሎጂስቲክስ ዘርፎች የሚሰሩ ተቋማት እንደሚሰማሩበት የሚገልፁት አቶ ካሚል፣ በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት በነፃ የንግድ ቀጣናው ከተመረቱ ምርቶች አምስት ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ መገኘቱን ይናገራሉ፡፡

ይሁን እንጂ ነፃ የንግድ ቀጣናው በነፃ የንግድ ቀጣና የአሰራር ሥርዓት መሠረት ሥራ አልጀመረም። በዚህም ምክንያት በነፃ የንግድ ቀጣናው ውስጥ በሥራ ላይ የሚገኙ ኩባንያዎች ሥራቸውን እያከናወኑ ያሉት በቀደመው የኢንዱስትሪ ፓርክ አሰራር ሥርዓት መሠረት ነው፡፡

አቶ አክሊሉ እንደሚናገሩት፣ ከስድስት ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ ባለሃብቶች ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር ስምምነት ተፈራርመው ሥራ ለመጀመር የሚያስችላቸውን የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅ መጽደቅን በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ፡፡ አዋጁ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተመርቷል፡፡ የነፃ የንግድ ቀጣናው በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ መግባት የዋጋ ግሽበትን በመቀነስ፣ የግብርና ግብዓቶችን አቅርቦት በማሳደግ፣ የኢንዱስትሪ ግብዓት ፍላጎትን በማሻሻል፣ የንግድና ሎጂስቲክስ አገልግሎቶችን በማቀላጠፍ ረገድ ለሀገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ አዋጁ በፍጥነት ጸድቆ ወደ ሥራ እንዲገባ ጥረት እንደሚደረግ ያስረዳሉ፡፡

አቶ ካሚል በበኩላቸው በቅርቡ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚጸድቀው የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅ በንግድና በሎጂስቲክስ ዘርፎች የሚሰሩ ተቋማት በነፃ የንግድ ቀጣናው ሥራ እንዲጀምሩ እንደሚያስችላቸው ጠቅሰው፣ ይህም በሀገር አቀፍ ደረጃ በሁለቱ ዘርፎች የሚታየውን ክፍተት ለመሙላት አቅም እንደሚፈጥር ይገልጻሉ። ‹‹በንግድና በሎጂስቲክስ ዘርፎች መሰማራት የሚፈልጉ በርካታ ባለሃብቶች ተመዝግበው እየጠበቁ ይገኛሉ፡፡ በንግድና በሎጂስቲክስ ዘርፎች እንደ ሀገር ትልቅ ክፍተት አለ፡፡ አዋጁ ሲጸድቅ ባለሃብቶቹ ሥራ ስለሚጀምሩ ይህን ክፍተት ለማስተካከል ይረዳል፡፡ በግብዓት አቅርቦትና በምርት ሥራ ሂደት ብዙ የሥራ እድሎች ይፈጠራሉ፤ የዋጋ ግሽበትን ለማረጋጋትም ያግዛል›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

ነፃ የንግድ ቀጣና ኢንቨስተሮች ገንዘባቸውን፣ እቃቸውንና እውቀታቸውን ይዘው የሚመጡበት የኢኮኖሚ ማዕከል እንደሆነ የሚገልፁት የ‹‹ኢፒክ ሶሉሽን›› ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሀቢብ አብዱልሃሚድ፣ የነፃ የንግድ ቀጠና አሰራርና ትግበራ ገበያን በማረጋጋትና እሴት በመጨመር ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ይናገራሉ፡፡ አሰራሩ ለምርት፣ ለግብይትና ለሎጂስቲክስ ሥራዎች የሚያስፈልገውን ጊዜ በማሳጠር ውጤታማ የንግድ እንቅስቃሴን እውን እንደሚያደርግ ጠቅሰው፣ የሕግ ማዕቀፎችን ዝግጅት በማጠናቀቅ ነፃ ንግድ ቀጣናውን በሙሉ አቅሙ ሥራ ማስጀመር እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ መምህር ዶክተር ሙሉጌታ ግርማ የሕግ ማዕቀፎች ዝግጅት በጥንቃቄ ሊከናወን እንደሚገባ ይመክራሉ። ‹‹የነፃ የንግድ ቀጠናዎች ትግበራ ራሱን የቻለ የሕግ ማዕቀፍ ያስፈልገዋል ሲሉ ጠቅሰው፣ በዚህ ሂደት ውስጥ አስቻይ ሁኔታዎችንና አማራጮችን በተረጋጋ ሁኔታ መገምገምና መመልከት እንደሚገባ አስታውቀዋል፡፡ የሕግ ማዕቀፎች በበቂ ጥናት ላይ ተመስርተው ካልተዘጋጁ ለሕገ ወጥ ንግድ መስፋፋት ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ተናግረው፣ እነዚህን ችግሮች አስቀድሞ መከላከል አስፈላጊ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ ለእዚህ ደግሞ በጥልቅ ምልከታ ላይ የተመረኮዘ የአሰራር መመሪያዎች ዝግጅት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

# ጎሜ

# ቢቻል መደገፍ ካልሆነ አለማደናቀፍ

እስማኤል አረቦ

እንደተለመደው ዘውዴ መታፈሪያ፤ ተሰማ መንግሥቴና ገብረየስ ገብረማርያም ማምሻ ግሮሰሪ ቁጭ ብለው ይጫወታሉ፡፡ በድንገት ከፊት ለፊት የተከፈተው ቴሌቪዥን የምሽቱን ዜና ማወጅ ጀመረ። ተሰማ መንግስቴ ‹‹እስኪ ዝም በሉ ዜና እየታወጀ ነው፤ እናዳምጥ ብሎ ››ጓደኞቹ ላይ ኮስተር አለ፡፡

ዘውዴ መታፈሪያም ‹‹አንተ ደግሞ ምን አዲስ ነገር ይኖራል ብለህ ነው፤ እባክህ የራሳችንን ጨዋታ ብንቀጥል ይሻላል ›› ብሎ ወደ ቀደመው ጨዋታ ለመመለስ ተዘጋጀ፡፡

በዚህ መሃል ኢትዮጵያ ለአራተኛ ጊዜ የዓባይ ግድብ ውሃ መሙላቷን የሚያበስር ዜና ተበሰረ። ቤቱ በጭብጨባና በደስታ ተሞላ፡፡ ዘውዴ መታፈሪያ ግን ‹‹ምን ዋጋ አለው፤ ውሃ መሞላቱ የኑሮ ውድነቱን አይቀንሰው›› የሚል ሃሳብ ሰነዘረ። ሁሉንም ነገር የማጣጣልና የማንኳሰስ አባዜ የተጠናወተው ዘውዴ ነገሮችን ከማድነቅ ይልቅ ቶሎ ብሎ የማናናቅ ባህሪ የተጠናወተው ነው። በዚህ ባህሪው ብዙ ጊዜ ከተሰማ መንግሥቴና ከገብረየስ ገብረማርያም ጋር አይስማማም፡፡

የዘውዴን አሉታዊ ሃሳብ ያዳመጠው ገብረየስ ስሜቱ በድንገት ቅይር ብሎ ‹‹አንተ ደግሞ መቼ ይሆን ነገሮችን በትክክለኛ ገጽታቸው የምትረዳቸው። ከዓባይ ግድብ በላይ ምን የሚያስደስት ዜና ኖሮ ነው ቶሎ ብለህ ወደ ነቀፌታ የገባኸው፡፡ የዓባይ ግድብ እኮ የመንግሥት ወይም አሁን ያለው የገዢው ፓርቲ ንብረት አይደለም። የሁላችንም አንጡራ ሀብት የፈሰሰበትና ውጤቱንም በጉጉት የምንጠብቀው ነው፡፡ በመንግሥት ሚዲያ ስለተነገረ ብቻ የመንግሥት አድርጎ መውሰድና ተቻኩሎም ለነቀፋ መዘጋጀት ተገቢ አይደለም፡፡

ሁልጊዜ ለምን በመጥፎ ዜና ውስጥ መዋኘት እንፈልጋለን፤ ለምን ጨለማውን ብቻ እየፈለግን መጓዝ እንሻለን፡፡ ሀገራችን እኮ የእኛው ናት። መከራዋ እንደሚያሸማቅቀን ሁሉ በደስታዋም ልንፈነጥዝ ይገባል...›› ብሎ ነገሩን ሳይጨርስ ዘውዴ መታፈሪያ አቋረጠውና ‹‹ወረድክብኝ እኮ፤ የዓባይ ግድብ የሁላችንም አይደለም አላኩም። ወይም ውሃ ሙሌት በመከናወኑ ተከፋሁም አልወጣኝም፡፡ ነገር ግን እኔ ያልኩት የኑሮ ውድነቱ ትኩረት ሳይሰጠው የውሃ ሙሌቱን እንደ ትልቅ ስኬት ልናየው አይገባም ማለቴ ነው›› ብሎ ሁለቱንም ተመለከተ፡፡

ተሰማ መንግሥቴ ወዲያው ቀበል አደረገና‹‹ ዘውዴ እባክህን ይህንን ባህሪህን ተው፡፡ ምንም ጥሩ ነገር ቢሰራ እና መልካም ነገሮች ቢበዙም አንተና መሰሎችህ የሚታያችሁ ጉድለት ነው፡፡ ሁልጊዜም ከሙላቱ ይልቅ ጉድለቱ ይታያችኋል። ነገሮችን በሚዛናቸው ከማየት ይልቅ ህጸጽ መፈለግ ላይ ታተኩራላችሁ፡፡ ይህ ደግሞ ጤንነታችሁን ከማወክ አልፎ ሌሎች ጥሩ ስሜት እንዳይሰማቸው እንቅፋት ትሆናላችሁ፡፡

አሁን በየማህበራዊ ሚዲያው የሞሉት ነገሮችን በሚዛናቸው መመልከት የተሳናቸው ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች የመንግሥት ባለስልጣናትም ሆኑ ሌሎች ታዋቂ ሰዎች የሚያስተላልፏቸው መልዕክቶች በቁንጽል በመውሰድ የመነጋገርያ አጀንዳ ለመፍጠር መሞከራቸው ነው፡፡ መልዕክቶችን ከተነገሩበት አውድ ውጭ ቀንጭቦ በመውሰድ ተናጋሪዎችን ለማብጠልጠልና ለማሳነስ ይሞክራሉ፡፡ ባልዋሉበት የስብሰባ አዳራሽ ወይም የውይይት ቦታ ተንታኝና ሚስጢር አዋቂ ሆነው ቁጭ ይላሉ።

ቅንጭብ ሃሳብ ላይ ተመስርተውም ሴራ ተንታኝና አዋቂ መስለው ይቀርባሉ፡፡ እነዚሁ የማህበራዊ ሚዲያ ጀግኖች እነሱ ያነሱት ሃሳብ ካልሆነ በስተቀር የሌላውን በማጣጣል ይታወቃሉ።

**አዳዲስ ሃሳቦችን ይሻሻሉ፤ ሌሎች ለመሥራት ሲደፍሩም ይኮንናሉ፡፡ የነበረው ድክመት፤ በመጥፎ አስተሳሰብ፤ ብልሹ አሰራር፤ ድህነት፤ ኋላቀርነትና ድንቁርና እንደነበረ እንዲቀጥል ይሻሉ። የማይጠቅሙ ሃሳቦች ሕዝብና ሀገር እየጎዱም ቢሆን እንዲቀጥሉ ይፈቅዳሉ**

በተለይ መንግሥት ሰራኋቸው የሚለካቸውን ልማቶች በሙሉ በማጣጣልና በዜሮ በማባዛት ‹ምን ዋጋ አለው› ሲሉ ይደመጣሉ፡፡›› ተሰማ ነገሩን እያስረዳ ባለበት ሰዓት ዜና አንባቢው ሌላ መረጃ እያስተላለፈ ነበር፡፡

ኢትዮጵያ በተያዘው ዓመት ስንዴን ሙሉ ለሙሉ ከውጭ ማስገባት እንደምታቆምና አልፉም ለውጭ ገበያ ለማቅረብ መዘጋጀቷን ዜናው አበሰረ፡፡ ወዲያው ዘውዴ መታፈሪያ ቀበል አድርጎ ‹‹ይኸው፤ የፈራሁት አልቀረም፤ ኑሮው ጣራ ነክቶ ስንዴ ለውጭ ገበያ ልናቀርብ ነው የሚለው ዜና እንዴት ሊያሳምነኝ ይችላል፤ በምንስ ፍጥነት ነው በአንድ ጊዜ ከተቀባይነት ወደ ስንዴ ላኪነት የምናድገው›› ብሎ ቀደም ሲል ያነሳው ሃሳብን የሚያጠናክር ማስረጃ ለማቅረብ ሞከረ፡፡

ገብረየስ ቀበል አድርጎ ‹‹ዘውዴ እኔ እኮ የምልህ ነገሩን መጀመሪያ በአግባቡ ሳታላምጥ አትዋጥ ነው። መጀመሪያ በአግባቡ አውጥተህ ካወረድክ በኋላ ነው መበየን ያለብህ፡፡ ግራ ቀኙን ሳትመለከትና በአግባቡ ጉዳዩን ሳትረዳ ቀድመህ ለመፈረጅ አትጣደፍ፡፡ አሁን አንተ ማብራሪያ መስጠት የጀመርከው እኮ ገና ጋዜጠኛው መረጃውን አስተላልፎ ሳይጨርስ ነው፡፡

እኔ እንደማስበው አሁን የተላለፈው መረጃ እውነት የማይሆንበት ምንም ምክንያት የለም። ኢትዮጵያ ሰፊ መሬት፤ በርካታ የሕዝብ ቁጥር ያላት፤ ተስማሚ የአየር ጸባይና ዓመቱን ሙሉ የሚፈሱ ወንዞች ያላት ሀገር ነች፡፡ ይህንን ሁሉ ሀብት ይዘን ስንዴ ከውጭ ማስመጣታችን ሊያሳፍረን በተገባ ነበር፡፡ እኛ ግን በስንፍናችን ተኩራርተን የሚሰሩ ሰዎች ሲነሳሱ እንኳን አይሆንም፤ አይሳካም፤ የሚሉ አሉታዊ ቃላትን በመደርደር ልናሳንፋቸው እንጣጣራለን፡፡ ስንፍናችን ልናጋባባቸው እንታትራለን፡፡

እስከ ዛሬ ስንዴን ወደ ውጭ አለመላካችን ወደፊትም ስንዴ እንደማንልክ አድርገን እንድናስብ ምክንያት ሊሆነን አይችልም፡፡ ስንፍናችን አንድ ቦታ ሲያቆምና የሚሰሩ አዕምሮዎችና እጆች ሲፈጠሩ ስንዴን አምርተን ከራሳችን አልፎ ለሌሎችም መላክ እንደምንችል ማሰብ እንዴት ተሳነን፡፡ ለምን ስንፍናችንን ዋስትና አድርገን መኖር እንፈልጋለን፡፡ ሌሎች ከተጠናወተን ስንፍና ሊያወጡን ሲሞክሩስ ከመደገፍ ይልቅ ማጣጣልን ለምን መረጥን፡፡

ኢትዮጵያ እንደ ስንዴው ሁሉ ለሩዝ ምርት ትኩረት በመስጠት ከሀገራዊ ፍጆታ አልፎ ለውጭ ገበያ ለመላክም እየሰራች ነው፡፡ በተለይም ሀገሪቱ ለሩዝ ምርት ተስማሚ የሆነ የአየር ጸባይና ምቹ መሬት ያላት መሆኑ ያቀደችውን ወደ ተግባር ለመለወጥ እንደማያዳግታት የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ እኔም ብሆን ወደ ፎገራና ጅማ አካባቢ በተጓዝኩበት ወቅት ያየሁት ይህንኑ ሀቅ ነው፡፡

የሩዝ ማሳው ተንጣሎ ሲታይ ነፍስን ይማርካል። ተስፋንም ያጭራል፡፡ ነገር ግን ይህንን ማየት የሚቻለው ዓይንን መክፈት እና ከጥላቻ ወጥቶ ነገሮችን በሚዛናቸው ማየት ሲቻል ነው፡፡ ብቻ ሁኔታችን በሙሉ የሚሰሩ ሰዎችን ማጣጣል፤ አዳዲስ አስተሳሰቦችን ማንቋሸሽ እየሆነብኝ ግራ ተጋብቻለሁ፡፡›› ብሎ ሃሳቡን አሳረገ፡፡

ተሰማ መንግሥቴ ተራውን ወሰደ፡፡ ‹‹ገብረየስ እንዳለው፤ አሁን ያለንበት ሁኔታ አሳሳቢ ነው። ከማድነቅ ይልቅ ማንቋሸሽን፤ ከማመስገን ይልቅ መንቀፍን፤ ወደ ላይ ከፍ ከማድረግ ይልቅ ማጣጣልን እንደ ባህል እየወሰድነው ነው፡፡ በተለይ በየማህበራዊ ዲው ምሁራን ነን ወይም በዘመኑ ቋንቋ ኤሊቶች ነን የሚሉት ሰዎች የሚሰሩት ለሀገር ጠንቅ እየሆነ ነው፡፡

በአሁኒቷ ኢትዮጵያ በየማህበራዊ ሚዲያው ቀን ከሌሊት ተጥደው የሚታዩት ‹‹ምሁራን›› እና ኤሊቶች ሁኔታ ደስ የሚል አይደለም። በእያንዳንዱ የዕለት ተዕለት ጉዳይ ሳይቀር ከመተማመን ይልቅ ጥርጣሬ፣ ከትብብር ይልቅ መገፋፋት፣ በግልጽ ከመነጋገር ይልቅ መተማማት፣ በማስረጃ ላይ ተመሥርቶ ውሳኔ ላይ ከመድረስ ይልቅ ባልተጣራ መረጃ መፈራረጅና የመሳሰሉት ከንቱ ነገሮች ጎልተው ይታያሉ፡፡ በማኅበራዊ የትስስር ገጾችና በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች በሚስተዋሉ ሽኩቻዎች ከሀገር አንድነት ይልቅ፣ ሀገርን ለመበተን የሚጎሻሸሙ ተቃርኖዎች ከመጠን በላይ በርክተው ይስተዋላሉ፡፡

ስለዚህም ነፍጥ ካነገቡ ጦር ሰባቂዎች ባልተናነሰ ሁኔታ አሁን በኢትዮጵያ ለሚታዩት ግጭቶች፤ አለመረጋጋቶች፤ ስደትና መፈናቀል ጥራዝ ነጠቅ ምሁሮቻችንና ኤሊቶቻችን የራሳቸውን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ ከእነሱ ስሜትና ሃሳብ በስተቀር የሀገር ጉዳይ የሚያገባቸው አይመስሉም፡፡

ከኢትዮጵያ ውጭ ሌላ ሀገር የለንም። ለኢትዮጵያ የሚሰራ መልካም ነገር ሁሉ ሊያስደስተን ይገባል፡፡ ወድቀቷና መነሷ ሊያሳምመንና ሊቆረቁረን ይገባል። ከግለሰብ እይታ ወጥነት ሀገራዊ እይታ ሊኖር ያስፈልጋል፡፡ ከእኔነት ይልቅ እኛነትን ማስቀደም የግድ ይላል፡፡

ኢትዮጵያ ከፊቷ የተጋረጡ በርካታ ችግሮች ያሉባት ሀገር ናት፡፡ የሀገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በሙሉ ለመነጋገርና ለመደማመጥ ጊዜ መስጠት አለባቸው፡፡ ጽንፍ ለጽንፍ ሆኖ ቃላት መወራወርና ይዋጣላን ማለት እንደሀገር ዋጋ አስከፍሎናል፡፡ በዚህም መንገድ ለዘመናት ተጉዘን ያተረፍነው ድህነትን፤ ኋላቀርነትና ዕልቂትን ብቻ ነው፡፡ እኔ የሚለው ሃሳብ በእኛ እስካልተተካ ድረስ መወነጃጀልና መወቃቀስ ብሎም እንደ ሀገር የሚሰሩ ሥራዎችን በሙሉ ማጣጣል አይቀርም፡፡

ስለሆነም የታሪካችን አንዱ ክፋይ ሆኖ ዘመናትን የተሻገረውን ጦርነትና ግጭትን ለማስወገድና የተረጋጋች፤ ሰላሟ የተጠበቀ እና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመጭው ትውልድ ለማውረስ ስሜታችንን ማረቅ ይገባል፡፡››ብሎ ሃሳቡን አሳረገ፡፡

ሲወቀስ የቆየው ዘውዴ መታፈሪያ በቅሬታ ስሜት ወደ ሁለቱም እየተመለከተ ‹‹ጓደኞቼ በዚህ መልኩ ስሜታዊ ትሆናላችሁ ብዬ አላሰብኩም። በርግጥ ያነሳችሁት ሃሳብ መሬት የሚወድቅ ነገር የለውም፡፡ ግን ደግሞ መንግሥት ክፍተቱን ካላሳየነው ሊማር አይችልም፡፡ ሁሉንም ነገር ትክክል ነህ ካልነው የበለጠ ሊሰራ አይችልም። ደግሞም እናንተም የማትክዱት በሀገራችን እየታየ ያለው ኑሮ ውድነት መኖር ከማንችልበት ደረጃ አድርሶናል። ይህንን መቼም እናንተም አትክዱም።›› ብሎ በአሸናፊነት ስሜት ተመለከታቸው፡፡

ገብረየስ ቀበል አደረገና ‹‹ዘውዴ፤ እኛ የኑሮ ውድነት የለም አላልንም፡፡ ነገር ግን የኑሮ ውድነት አለ በሚል ሌሎች ሥራዎችን አብሮ ማጣጣሉና ማጠልሸቱ ይቁም ነው እያልን ያለነው፡፡

ደግሞም እኮ፤ የኑሮ ውድነቱን መቅረፍ የምችለው በማጣጣልና በማንቋሸሽ አይደለም። የስንዴም ሆነ የሩዝ ልማቱ አልያም ሕዳሴ ግድብ ውሃ ሙሌት ዞሮ ዞሮ የእኛን ኑሮ ለማቅለል የሚደረጉ ጥረቶች ናቸው፡፡

ብዙዎች ከመሥራትና ያለውን የኑሮ ውድነት ለማቋቋም የሚያስችላቸውን አቅም ለመገንባት ከመጣጣር ይልቅ ሲያማርሩ ውለው ማድረን ይመርጣሉ፡፡ ጉልበታቸውን፤ እውቀታቸውንና ገንዘባቸውን አሉታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያባክናሉ፡፡

ይባስ ብሎም ሊሰሩ የሚነሳሱ ሰዎችን ያንቋሽሻሉ፡፡ ይተቻሉ፤ ይወቅሳሉ፤ አልፎ ተርፎም ያብጠለጥላሉ፡፡ እነሱ መሥራት ያልቻሉትን ነገር ሌሎች ሲሰሩ እንደመደሰት በተቃራኒው ይከፋሉ፡፡ አብሮ ከማደግ ይልቅ አብሮ መውደቅን ይመርጣሉ።

አዳዲስ ሃሳቦችን ይሻሻሉ፤ ሌሎች ለመሥራት ሲደፍሩም ይኮንናሉ፡፡ የነበረው ድክመት፤ በመጥፎ አስተሳሰብ፤ ብልሹ አሰራር፤ ድህነት፤ ኋላቀርነትና ድንቁርና እንደነበረ እንዲቀጥል ይሻሉ። የማይጠቅሙ ሃሳቦች ሕዝብና ሀገር እየጎዱም ቢሆን እንዲቀጥሉ ይፈቅዳሉ፡፡

መሻሻል፤ መለወጥ፤ መታደስ የሚሉ ተስፋ ሰጪ ሃሳቦችን ይፈራሉ፡፡ እነዚህን ሃሳቦች አንግበው የሚነሱ ሰዎችን በተቻላቸው መጠን ተረባርበው ለማጥቃትና ለማሸማቀቅ ይጥራሉ። በጎ ሃሳቦችን በእንጭጫቸው ለመቅጠፍ ይታትራሉ። በአጠቃላይ እነዚህ ሰዎች በሕይወታቸው ተስፋ የቆረጡና ኑሯቸውም ከእለት ተዕለት ፈቀቅ የማይል ነው፡፡

በራሳቸው አሉታዊ ገመድ የታሰሩ በመሆናቸውም የሚፈታቸው አንዳችም ምድራዊ ኃይል የለም፡፡ ያላቸው ጉልበት፤ አቅምና ችሎት ግን የሚሰሩ ሰዎችን ማጣጣል፤ ማጠልሸት፤ መንቀፍና ማዋረድ ነው፡፡

እራሳቸው ጎዶሎ ስለሆኑ ሌሎችንም ማጉደል ይፈልጋሉ፡፡ እራሳቸው በሁለት እግራቸው መቆም ስለማይችሉ ሌሎችም አንካሳ እንዲሆኑ ይመኛሉ።

እራሳቸው ብርሃን ስለማይታያቸው ሌሎችም ጨለማ ውስጥ እንዲዘፈቁ ታትረው ይሰራሉ፡፡ ሌሎች ሰርተው እንኳን እንዳያወጣቸው መልካም ሥራዎችንና ሃሳቦችን ለመቁረጥ ምሳር ይዘው ይነሳሉ፡፡ ለሀገር ለወገን የሚጠቅሙ ሃሳቦችን ከራሳቸው ግላዊ አመለካከት ጋር በማወዳደር ከጥሩ ሃሳቦች ጋር ይገዳደራሉ፡፡››ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ፡፡

በተሰማ መንግሥቴ ፊት ላይ እርካታ፤ በዘውዴ መታፈሪያ ገጽ የተሸናፊነት ስሜት ረበበ።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## ካታካምቡ በ‹‹ሀሁ ወይም ፐፑ››

ሙሉጌታ ብርሃኑ

"ሀሁ" ወይም "ፐፑ"... ታላቁ ደራሲ ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድህን ከዛሬ ሰላሳ ዓመታት በፊት ከካታካምቡው አስፈሪ ዋሻ መሃል አምጦና ወልዶ ለመድረክ ያበቃው ከምርጥ የዘመናችን የመድረክ ተውኔት ሥራዎች መሃከል አንደኛው ነው። "ሀሁ" ወይም "ፐፑ" በሁለት የተለያዩ መንግሥታት ማብቂያና መጀመሪያ፤ በአመሻሽና ንጋት፤ በካታካንቡው ዋሻ በቆሙ ሁለት የፖለቲካ አንበሶች መሃከል ተቀምጦ የጻፈው ቲያትራዊ ተውኔት ነው። ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድህን ይህን ቲያትራዊ ተውኔት ለመድረክ በ1984ዓ.ም ቢሆንም የጻፈው ግን ቀደም ሲል የደርግ መንግሥት ማብቂያ ደወል ማቃጨል ከጀመረበት ከ1982 ዓ.ም መጨረሻዎቹ ጀምሮ ነበር።

ቲያትሩ "ከእሳት ወይ አበባ" እና "ከሀሁ በስድስት ወር" የቀጠለ ተውኔት ነው። ዛሬ ይህን ጉዳይ ማንሳታችን ጥበበኛውንም ሆነ ይህን ድንቅ ተውኔት በአድናቆት ለማስታወስ ብቻም አይደለም። ይልቁንም በጊዜው በብዙ ጭንቅ አሳር ለመጀመሪያ ጊዜ ከብሔራዊ ቲያትር መድረክ ላይ ወጥቶ ለማደግ ባደገደገበት በዚያው መድረክ ላይ በቆመጥ እንዳይድን እንዳይሽር አድርጎ የመቅጨት ሙከራ ተደርጎበታል። እናም ሸሽቶ ከተደበቀበት ከብዙ ዝምታዎች በኋላ ዛሬ ተመልሶ የብሔራዊ ቲያትርን ደጅ ሲጠና የገጠመው አንድ ጉዳይ አለ። አሁን ጸጋዬ ገብረ መድህን የለም፤ የያኔው አዘጋጅ የነበረው ዓለሙ ገብረአብም እንዲሁ አሁን ከ"ሀሁ ወይም ፐፑ" በስተጀርባ የለም፡፡ አሁን በአዘጋጅነት የቀረበው ሰው ተስፋዬ ሲማ ነው፡፡ ቲያትሩ እትብቱ ወደ ተቀበረበት የብሔራዊ ቲያትር ለመግባት በመሰናዳት ሳለ ሌላ የግምገማና የፍተሻ ኬላ ገጥሞታል፤ ለምን?

"ሀሁ" ወይም "ፐፑ" ሰው ቢሆን ኖሮ ከተወለደባት ጊዜ አንስቶ ያነባው እንባ ዛሬም ድረስ ከዓይኖቹ ላይ ባልደረቀ ነበር። በወጌሻ የማይታሸው የልቡ ስብራትም ሳይጠገን በዓመታት ተሸፍኖ ጠባሳው ሳይሽር ጠቋቁሮ ነጠብጣቦችን እንደያዘ ዛሬ ላይ ደርሷል። "ሀሁ" ወይም "ፐፑ" ቲያትር ብቻ አይደለም። በኢትዮጵያ የመድረክ ሥራዎችም ሆነ በሌላ እስከዛሬም ድረስ ወሰን የሰበረበት ሌላ ድንቅ ታሪክ አለ። ይሄውም በዚህ ቲያትር ዙሪያ የሚያትተው "ምስጢረኛው ባለ ቅኔ" የተሰኘው ከአራት መቶ በላይ ገጾች ያሉት መጽሐፍ ነው። በዚህን ያህል ደረጃ ሂሳዊ ዳሰሳ የተጻፈለት ተውኔት በሀገራችን አንድም የለም።

ታሪኩ በጊዜ ፈረስ አስቀምጦ የኋልዮሽ ያስጋልበናል። የሚያደርሰው እንጂ የማይዋጋው የጊዜ ፈረስ ከ1980ዎቹ ላይ አሳርፎ በፖለቲካ ጦር የተወጋውን ቁስለኛ ቲያትር ከነሰቆቃው ያስመለከተናል። ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድህን ሥራዎቹ እሳትም አበባም ነበሩ። "እሳት ወይ አበባ" እንዳለው እሳትን መሆን የመረጠ ይመስላል፡፡ በጊዜው በተለያዩ ሥርዓቶች ውስጥ በማን አለብኝ የፖለቲካ ዙፋን ላይ ተቀምጠው ሕዝቡን ቁልቁል ለሚመለከቱ አንዳንድ ባለሥልጣናትና ሹማምንት ሥራዎቹ ከእሳትም የእግር እሳት የነበሩ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በእነርሱ ግፍ እየተብከነከነ አንጀቱ ለሚያረው ምስኪን ሕዝብ... አንጀት አርስ የተስፋ አበባዎች ነበሩ። ከእነዚህም አንዱ የስቃይ ገፈት ቀማሽ የሆነው "ሀሁ ወይም ፐፑ" የመድረክ ቲያትር ነው። በደርግ መንግሥት የስልጣን መባቻ ላይ የተጻፈው ይህ ቲያትር አብዮቱ በተገረሰሰ በዓመቱ በ1984ዓ.ም እራሱን አስተዋውቆ ወደ ጥበብ መንደር ተቀላቀለ።

በውስጡ የሚገኙት የገጸ ባህሪያቱ ውክልናና የታሪኩ ውልደት አብዛኛዎቹ ከአብዮታዊው የፖለቲካ ማህጸን ውስጥ የተገኙ ናቸው። ከወዲህ ማዶ የደርግ መንግሥት ቀኑ እየጨለመ ሰማይ በላዩ ላይ ለመደፋት ሲያዘቀዝቅ፤ ከወዲያ ማዶ ደግሞ የወያኔ የጦር ሠራዊት መላ ቅጡን ባጣውና ከየአቅጣጫው በተከፋፈተው የደርግ መንግሥት አጥር እየዘለለ ለሕዝቡ ሌላ የንጋት ማብሰሪያ ነጋሪቱን ለመጎሰም በመሰናዳት ላይ ሳለ፤ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድህን ግን በመሃል ከድልድዩ ስር ቁጭ ብሎ የሚሄደውንም እየመጣ ያለውንም ከመነጽሩ በታች አጮልቆ እየተመለከተ "ሀሁ ወይም ፐፑ"ን በመጻፍ ላይ ተጠምዶ ነበር። እግሬ አውጪኝ ሲል እየፈረጠጠ ያለውን ብቻ ሳይሆን ለመድረስ እግሩ አጥሮ እየገሰገሰ በመምጣት ላይ ያለውንም ደህና አድርጎ ተመልክቶት ነበርና ቲያትሩም በሁለት ሥርዓቶች መሃከል በተፈጠረው ትልቅ ገደል አንድ እግሩ ከወዲያ ማዶ ሌላኛውም ከወዲህ ማዶ እረግጦ በጽናት ቆመ። ቆሞም እንዲህ ሲል አሰበ፤ 'ሀሁ ብሎ በመጀመር ወይንስ ፐፑ ብሎ በመጠናቀቅ ላይ ይሆን?' ወሳኙ ጥያቄ ይሄው ነበር። አብዮቱ ተፈረካክሶ በአዲሱ መንግሥት ጅማሮ ውስጥ የታሪክ ፍርስራሽ መሆን ከጀመረ በኋላ የጥያቄውን ምላሽ ለማግኘት እምብዛም ጊዜ አልፈጀም ነበር።

የ"ሀሁ ወይም ፐፑ" የታሪክ ሰንሰለት ጅማሮውን የሚያደርገው እዚህ ጋር ነው። በ1984ዓ.ም የመጀመሪያዎቹ ወራት አካባቢ ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድህን የቲያትሩን ምናባዊ ቁመና በማጠናቀቅ የቲያትሩ አዘጋጅ ከሆነው ዓለሙ ገብረአብ ጋር በመሆን ለመድረክ ለማብቃት ተሰናዱ። የዚህን ጊዜ ወደ ብሔራዊ ቲያትር ጎራ ማለቱ ግድ ነበር። ቲያትሩ በብሔራዊ ቲያትር መድረክ ላይ እንዲታይ ፈቃድ ካገኘ በኋላ የቲያትር ቤቱ አስተዳደር ሃሳቡን እንደገና ለውጦ፤ ዳግም በኮሚቴ ካልተገመገመ ሲል ያለፈውን ውድቅ አደረገው። በኮሚቴ መገምገም አለበት የሚሉት ሌላ የማይወጣበትን የሳንሱር ቀንበር ለመጫን መሆኑ ነው...ጸጋዬ ግን ሃሳባቸው ምን እንደሆነ አስቀድሞ ገብቶታልና እነርሱን አልፎ በቀጥታ ወደ ባህል ሚኒስቴር በማምራትና ከባለሥልጣናቱ ጋር በመነጋገር ቲያትሩ እንዲታይ ፈቃድ አገኘ።

ነሐሴ 24 ቀን 1984ዓ.ም መሰናክሉን ሁሉ አልፎ ለመጀመሪያ ጊዜ ቲያትሩ ለመድረክ በቃ። በፖለቲካ ብሶት ልቡ የሳሳው የጥበብ ባለሙያና ተመልካቹ ሁሉ ይህን ቲያትር እየተመለከተ በእንባ መራጨት ጀመረ። ብሶት የወለደው እንባ... በሳምንት ለሦስት ቀናት የሚታይ ሲሆን ብሔራዊ ቲያትር ከአፍ እስከ ገደፍ በተመልካች ጎርፍ እየተጥለቀለቀ የማየት እድሉን አጥቶ የሚመለሰውም ብዙ ነበር። በውስጡ የሰላም ናፍቆትና ረሃብ የተሰነቀረበት ምስኪን ሕዝብ ቲያትሩን ሲመለከት ከውስጡ እየገነፈለ እንባ ከዓይኑ መፍሰስ ሆነ። የቲያትሩን እምቅ ሃሳብና የተመልካቹን ሕዝባዊ ስሜት ያጤኑት አዳዲሶቹ ሹማምንት ድባቡ ፈጽሞ ምቾትን አልሰጣቸውም ነበር።

ገና ወደ መድረክ ከመውጣቱ ጀምሮ ዓይናቸውን ጥለውበታል። ጸጋዬ ገብረ መድህን በአንድ ወቅት እንደገለጸው ከሆነ ይህን ቲያትር እንዲያቆም፤ በየጊዜው በስልክ የሚደርሱበት ዛቻና ማስፈራሪያዎችም ጭምር ነበሩበት። "ሀሁ ወይም ፐፑ" ቲያትርን በመድረክ ላይ ለማሳየት ሲወስን፤ አላማው የሀገሪቱን መንሸራተትና የሕዝቡን ጭቆና ማሳየት ብቻ አልነበረም፤ አዲስ የዴሞክራሲና የነጻነት ብርሃን በርቷል የሚለውንም ለማሳየት ጭምር ነበር። ነገሩ ግን የተገላቢጦሽ አቅጣጫውን ስቶ፤ አዲሱ መንግሥትም እርሱ እንደተመኘው የብርሃን ሳይሆን ሌላ የተጋረደ የጨለማ ሰማይ ከላዩ ላይ ዘረጋበት።

ስለ ቲያትሩ ካወጋን አይቀር ከውስጡ ጥቂት ሃሳቦችን ቦጨቅ ማድረጉ መልካም ነው። የቲያትሩ ጭብጥ በግርድፉ ሰላምን፣ ፍቅርን፣ ሀገራዊ አንድነትን፣ መተጋገዝን፣ የኢትዮጵያን ከፍታና ሰው የመሆንን ክብር ተደግፎ የሚያዘግም ሲሆን በሌላኛው ጎኑ ደግሞ የኢትዮጵያን ከከፍታው የመንሸራተትና የፖለቲካውን እድፍ በመንቀስ የከረፋውን እጣቢ ለመድፋት ሲፍጨረጨር እንመለከትበታለን። በዋናነት በሁለት ገጸ ባህሪያት ላይ ትኩረቱን አድርጓል። ለእውነት ሸንጡን ገትሮ በቆመው ታጋይ ነጋና በከተማው ጩልሌ በቢ አራጋው መሃከል፡፡ ብልጣ ብልጡ ከተሜ፤ ጸጉር ከምላሱ የሚነቅል፤ እንደ ምጣድ ላይ ቂጣ በሁለቱም በኩል እየተገለባበጠ በአንደበቱ ቅቤ የሚያነግት ስውር ስለት ነው። ቢሰማ ምንም አያመጣም ብሎ ባሰበው ሰው ፊት እንዳሻው ያሻውን ሁሉ ያወራል። እንዲያውም በደርግ ጊዜ አግበስብሶ የያዛቸው በርካታ ቤቶች በከተማው ውስጥ እንዳሉት በመናገር፤ "አሁንም ቢሆን ገና መላዋን አዲስ አበባ ከተማ አከራይቼ ስንትና ስንት ገንዘብ እሰበስባለሁ" ሲል ሌብነቱን እንደ ጀብዱ ሲያወራም እናደምጠዋለን። ማሸርገድና አፈ ቀላጤነቱ የተካነበትና ጥርሱን የነቀለበት በመሆኑ በታጋይ ነጋ ፊት ሲሆን የለውጡ ደጋፊና ተቆርቋሪ በመምሰል ዓይኑን በጨው አጥቦ ምላሱን ቅቤ ይቀባል። እውነታው ግን ለውጡን የማይደግፍና ፀረ-ኢህዴጋዊ አብዮተኛ መሆኑ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ዳንኬረኛ ሌንሳ፤ ዳንኬረኛ ግደይና ዳንኬረኛ እሙ ይህ እባብ እንዳይተናኮላቸው ይሠጋሉ። "ያን የቀበሌ ሊቀመንበር ታጋይ ነጋ ይሄን ያህል ቤት ከነዋሪዎች ላይ ቀምተህ እንድታስረክበኝ ብሎሃል በለው፡፡ ይህን ትዕዛዝ በፍጥነት ሳይፈጽም ቢቀር ምን ዓይነት ርምጃ ለመውሰድ እንደምንገደድም በደንብ አስረዳው እሺ!?" በማለት ለጀሌዎቹ ትዕዛዙን ሲያስተላልፍ እናደምጠዋለን። ታጋይ ነጋን ጨምሮ ሁሉም እርሱን ለመለወጥና እውነተኛ ማንነት እንዲኖረው ለማድረግ ሲጥሩ የሚያሳዩ ትዕይንቶችንም እንመለከታለን።

"ሀሁ ወይም ፐፑ" ከብሔራዊ ቲያትር ለአንድ ዓመት ያህል ዘለቀ፡፡ ከአንድ ዓመት የመድረክ ቆይታ በኋላ ግን በ1985ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በየትኛውም የቲያትር ቤት ውስጥ እንዳይታይ ታገደ። በዚህ ተስፋ ያልቆረጡት የቲያትር ቡድኑ አባላት ፊታቸውን ወደ ክልል ከተሞች አዞሩ። 1985 በተከለከለበት በዚያው ዓመት ቲያትሩን ለማሳየት ወደ ዲላ ከተማ አቀኑ። ዝግጅታቸውን አጠናቀው የመድረክ ቲያትሩ በመታየት ላይ ነበር። እንደተለመደው ተመልካቹም በስሜት ባህር ላይ ሰጥሟል። ከብዙ ትዕይንቶች በኋላ ከቲያትሩ አጋማሽ ላይ ግን አንድ ያልተጠበቀ ነገር ተከሰተ። ማንነታቸው በውል የማይታወቅ ጥቂት የማይባሉ አካላት ከተመልካቹ መሃል ብድግ በማለት ዱላና ቡጢያቸውን እየጨበጡ በፍጥነት ወደመድረኩ አመሩ። ያገኙትን እቃ በሙሉ እየሰባበሩ በቲያትር አባላቱ ላይ የዱላ መአት ማዝነብ ጀመሩ። በቲያትሩ ውስጥ ያልተጻፈና አዘጋጁም የማያውቀው ሌላ አስፈሪ ትዕይንት ታየ። ከመድረኩ የተዘረረው ብዙ ነው። ሁካታና ትርምስ በተሞላበት አዳራሽ ውስጥ ተመልካቹም ነብሱን ለማስመለጥ እግሬ አውጪኝ ሲል መተራመስ ሆነ። የተጎዱት አባላት ወደ ዲላ ሆስፒታል ተወስደው ታክመው መዳን ቻሉ።

በዚህ አልተገቱም ካገገሙ በኋላ እንደገና በሀዋሳ ከተማ ቲያትሩን ለማሳየት ዝግጅታቸውን ቀጠሉ። በሀዋሳው መድረክም በተመሳሳይ ሁኔታ የቲያትሩ ትዕይንት መታየት ጀመረ። ለሰላሳ ደቂቃዎች ያህል ከታየ በኋላ ድንገት ማዕበሉ ተቀሰቀሰ። ልክ ዲላ ላይ እንደነበረው በተመሳሳይ ገቢራዊ ትዕይንት፤ ወንበዴዎቹ ከተመልካቹ መሃል ብቅ ብቅ እያሉ የፊልም ትዕይንት አስመሰሉት። በዚህኛው ዙር፤ ዱላው ለቲያትር አባላቱ ብቻ ሳይሆን ለተመልካቹም ጭምር ሆነ። የወደቀው ወደቀ፤ያመለጠውም አምልጦ ብዙዎቹ ተጎዱ። መልእክቱም "ሀሁ ወይም ፐፑ"ን ያየህ ተቀጣ ነበር።

"ሀሁ ወይም ፐፑ" በኛ ዘመን...በኛ ጊዜ ከሰሞኑ ምን ገጠመው? ዳግም ወደ ብሔራዊ ቲያትር ብቅ ብሎ ነበር። ቲያትሩ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው በመሆኑ ከቲያትር ባለሙያ ይልቅ በሌላ አካል መገምገም አለበት የሚል ነገር ተነስቶበታል። በርግጥ በ2016 ሆነን 1984'ን መድገም ነበረብን ወይ? ጥያቄው ጥያቄ ብቻ ነው። ዛሬያችንን መሸሽ ትላትናችንንም መደበቅ አንችልም። ይህ ቲያትር ካለፈው ትላንት ተምረን ያለንበትን ዛሬን እንድናሳምር ያደርገን ይሆናል እንጂ ስጋትስ አይሆንብንም ነበር። ጉዳዩ እንደተባለው ከሆነ፤ በአሁኑ ሰዓት የምንመለከታትን የኪነ ጥበብ ሥራ የነጻነት ብልጭታ ጭራሹን ድርግም ብላ እንድትጠፋ ማድረግ ይሆናል። አልፈው የሚመጡ ነገሮች እስከሌሉ ድረስ ሙያውን ለባለሙያው መተው አስፈላጊ ነው። "ሀሁ ወይንም ፐፑ" ዛሬም ከመድረክ ላይ ሊያዩት የሚናፍቁ በርካቶች ናቸው። የጥበብ አምባሳደር የሆነው የብሔራዊ ቲያትርም በታሪካዊው ተውኔት ታሪካዊ ዐሻራውን ባማረ መልኩ ማሳረፍ አለበት።

"እኛ የዓለም እዳ ነን። ኒውዮርክና ፓሪስ የተገነቡት እኮ በኛ በአፍሪካውያን አጥንትና ደም ነው... ዘለዓለማችንን ከችግር የማንወጣ አሳዛኝ ተመጽዋቾች ሆነናል። ...እና ዝም ብለን፤ ቁጭ ብለን በረሃብ እንለቅ?... ሳንሰራ ቁጭ ብለን ብቻ?... ሰለጠን ስንል ሰየጠን... ተከባብረን ተቻችለን እናልፈዋለን ወይንስ ሰይጥነን እርስ በርሳችን እንተላለቃለን? ሰዎች ሕልማችሁ ምንድነው?" ይለናል፤ ጸጋዬ በቲያትሩ ውስጥ። ሀሁ ተስፋ ነው። ሀሁ አዲስ ንጋት ነው። ሀሁ የዴሞክራሲ መጀመሪያ ነው። በተቃራኒው ደግሞ ፐፑ ከትላንት በባሰ መሸራተት፤ ከድጡ ወደ ማጡ ቁልቁል የሚያሽቆለቁለን አስፈሪ የካታካንቡ ዋሻ ነው። ሀሁ ወይንስ ፐፑ?



ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የአካል ጉዳተኛውን ችግር ለማቅለል የተቋቋመው ማዕከል

**እዮሩስ ተስፋዬ**

አካል ጉዳተኛነት በተፈጥሮ እና በሰው ሠራሽ ችግሮች ሊመጣ እንደሚችል እሙን ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን በየጊዜው በሚከሰተው የመኪና እና መሰል አደጋዎች፣ በግጭት እንዲሁም በሌሎች ሰው ሠራሽ ችግሮች ምክንያት የአካል ጉዳተኛው ቁጥር ከፍ ሊል እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ አካል ጉዳተኞቹ ሰው ሠራሽ የአካል ድጋፍ በቀላሉ ማግኘት ስለማይችሉ ሊሠሯቸው ከሚፈልጓቸው ነገሮች እንዲቆጠቡ መገደዳቸው ደግሞ ችግሩን የከፋ ያደርገዋል፡፡

አሁን ላይ ግን እንዲህ ዓይነቱን ችግር ለማቅለል "የኢትዮጵያ የአካል ድጋፍ አገልግሎት ማዕከል" በይፋ ተመርቆ ለበርካቶች ለመድረስ ሥራውን ጀምሯል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በማኅበራዊ ትስስር ድረ-ገጻቸው ላይ እንዳሰፈሩት "መሥራት፣ ማገልገልና መስጠት እየቻሉ በተለያዩ የአካል ጉዳቶች ሕክምና ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች የሚሆን እንደ አዲስ የተደራጀውን የኢትዮጵያ የአካል ድጋፍ አገልግሎት ማዕከልን ዛሬ ተመልክተናል፡፡ ለኢትዮጵያ ከዚህም በላይ ትልቅ ተቋም ያስፈልጋታል"፡፡

ማዕከሉ በተፈጥሮ እና በአደጋ ምክንያት የአካል ጉዳተኛ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች በሀገር ውስጥ አጋዥ ቁሶችን ለማምረት እና ለማቅረብ የተቋቋመ ማዕከል ነው፡፡ በተጨማሪም ማዕከሉ አጋዥ ቴክኖሎጂዎችን ለማምረት፣ ለማደስ እና ለማቅረብ የተቋቋመ ሲሆን፤ ተደራሽ፣ ጥራት ያለው እና ደንበኛ ተኮር የሰው ሠራሽ እንዲሁም የአካል ድጋፎች አገልግሎትን ለኅብረተሰቡ የሚሰጥ እንደሚሆን ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

በተለያዩ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች የተሻለ ሰው ሠራሽ የአካል ድጋፍ የሚያቀርብ ተቋም መገንባቱን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ብዙውን ጊዜ በቂ ትኩረት ስለማያገኙ ማገልገል እየቻሉ ተረጂና ተመጽዋች የሚሆኑ ዜጎች መኖራቸውን አስታውቀዋል፡፡ መንግሥት አካል ጉዳተኞችን የሚያስታውስ ሥራ እናከናውን ብሎ ሲነሳ ብቁ ባለሙያዎች ቢኖሩም፤ በዘርፉ በቂ ግብዓት የተሟላላቸው ተቋማት እንዳልነበሩ በማውሳት፤ አሁን ላይ ዘመናዊ መሣሪያዎች ያሉትና ይበልጥ የተማሩ ባለሙያዎች የታከሉበት፤ እንዲሁም፣ አካል ጉዳተኞችን በማገዝ ረገድ ሰፊ ሥራ የሚከናወንበት ማዕከል መገንባት እንደተቻለ አስረድተዋል፡፡



በኢትዮጵያ የአካል ድጋፍ አገልግሎት ማዕከል ድጋፍ ከተደረገላቸው መካከል

በጦርነትም ሆነ በተለያዩ አደጋዎች እጃቸውን አሊያም እግራቸውን ያጡ ዜጎች በማዕከሉ ገብተው አጋዥ አካል ወይም ሰው ሠራሽ አካል ተገጥሞላቸው የሚንቀሳቀሱበትና ማገልገል የሚችሉበት ዕድል እንደተፈጠረላቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ የገለጹ ሲሆን፤ ማዕከሉ በቀጣይ በተለያዩ አደጋዎች ምክንያት የጆሮ ማዳመጥ ችግር እና የማየት ችግር ያጋጠማቸውን ዜጎች ጭምር ማገዝ የሚችልበትን አቅም እንዲያገኝ፣ ተቋሙ በቴክኖሎጂ አማካኝነት ዓይነ ስውራንን የሚያግዙ መነጽሮችን ወደ መሥራት ማደግ እንዳለበት አሳስበዋል።

ታካሚዎች በተቋሙ ለሕክምና በሚንቀሳቀሱበት ወቅት አዕምሯቸውን የሚያድሱ አረንጓዴ መናፈሻዎች፣ የስፖርት ማዕከላትና ልምምድ የሚሠሩባቸው ንጹህ ስፍራዎች የተገነባ መሆኑን ሲያስረዱም «የሰው ልጅ ከአካል ስብራቱ ይልቅ ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስደው የአእምሮ ስብራቱ ነው፡፡ አእምሯችን ሲጎዳ ነፀብራቁ አካላችን ላይ ስለሚታይ መንፈስን የሚያድሱ መሠረተ ልማቶች ናቸው፡፡» በማለት የማዕከሉን ውብነት ገልጸዋል፡፡

በማዕከሉ ግንባታቸው የተጠናቀቁ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረጊያ ስፍራዎች ማለትም የመዘናኛ ስፍራ፣ የአካል ድጋፍ ማምረቻ እና የፊዚዮቴራፒ መስጫዎች ተገንብተዋል። የማዕከሉን አገልግሎት ማሳደግ ከተቻለም ከኢትዮጵያ አልፎ እና ተርፎ ለአፍሪካም ጭምር በዘርፉ አጋዥ የሆነ ሥራ ለማከናወን መነሻ የሚሆን ማዕከል መሆን ይችላል፡፡ የኢትዮጵያ አካል ድጋፍ አገልግሎት ማዕከል በቴክኖሎጂ በታገዘ መንገድ ጥራት ያለውና ደንበኛ ተኮር የሰው ሠራሽና የአካል ድጋፍ አገልግሎቶችን ለኅብረተሰቡ እየሰጠ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልጸዋል፡፡

የጤና ሚኒስትር ዶ/ር ሊያ ታደሰ በበኩላቸው ብሔራዊ የአካል ድጋፍና ተሃድሶ ስትራቴጂ ተቀርጾ ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን፤ በተለያዩ ምክንያቶች አገልግሎት መስጠት ያቆሙ የተሃድሶ ማዕከላት ዳግም ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከዚህ አኳያም በጥቁር አንበሳ፣ ሀረር እና ጋምቤላ ሆስፒታሎች የነበሩ የተሃድሶ ማዕከላት ዳግም አገልግሎት መስጠት እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ የአካል ድጋፍ አገልግሎት ማዕከል ሁሉን አቀፍ ጥራቱን የጠበቀ የተሃድሶ ሕክምና እና የአካል ድጋፍ አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችለው በማዕከሉ የሰው ኃይል በማቅረብ፣ መሳሪያዎችን በማሟላት እና ከተለያዩ አካላት ድጋፍ እንዲያገኝ በመደረጉ በአሁን ወቅት ለበርካቶች አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

በሀገራችን በተለያዩ አደጋዎችና ሁኔታዎች ምክንያት ለሚከሰት አካል ጉዳተኛነት የአካል ድጋፍ አገልግሎትን ለማሳደግና ችግሩን ለማቅለል ሲባል ከዚህ ቀደም ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ጀርባ ለበርካታ ዓመታት ቀደም ባለ ቴክኖሎጂ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረውን ተቋም በብዙ መልኩ በአዲስ መልክ በማዘመን የኢትዮጵያ አካል ድጋፍ አገልግሎት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በ2014 ዓ.ም መቋቋሙን ዶ/ር ሊያ አስታውሰዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደገለጹት፣ ማዕከሉ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የሆነ እና ለሌሎች ፕሮጀክቶች ተምሳሌት የሚሆን ነው። ሌሎች ፕሮጀክቶችም አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉ መሆን ያለባቸው ሲሆን፣ ይህንን ያላካተቱ ነባር ፕሮጀክቶች ደግሞ እንደገና የማሻሻል ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ ማዕከሉ ከዚህ ቀደም ከውጭ የሚገቡ አካል ድጋፍ ቁሳቁሶችን በራሱ አቅም ማምረት መጀመሩ ትልቅ እምርታ እና ለአካታች የጤና አገልግሎት ተደራሽነት መሻሻል ሚናው የጎላ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

አካል ጉዳተኞች ምቹ ሁኔታዎችን እና ድጋፍ ባለማግኘታቸው ምክንያት ከበርካታ ተሳትፎዎች እንዲወሰኑ ያደርጋቸዋል ያሉት ከንቲባዋ፣ በቀጣይም አካል ጉዳተኞችን ያማከለ ሥራ በስፋት መሥራት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ኤክስ የቆዩ እና አገልግሎት ያቆሙ አካውንቶችን ሊሸጥ መሆኑ ተነገረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ኤክስ የቆዩ እና አገልግሎት ያቆሙ አካውንቶችን ሊሸጥ መሆኑ ተነገረ።

የኤክስ ማህበራዊ ሚዲያ ወይም የቀድሞው ትዊተር የቆዩ እና አገልግሎት መስጠት ያቆሙ አካውንቶችን ለመሸጥ በሂደት ላይ መሆኑ ተገልጿል።

እንደመረጃው ከሆነ ኤክስ አንዱን አካውንት በ50 ሺህ ዶላር ለመሸጥ አስቧል።


ይህ ባለፈው ዓመት እንደተጀመረ የተገለጸው እንቅስቃሴ ጎልቶ የወጣው የሽያጭ ጥያቄዎች ሊገዙ ይችላሉ ለተባሉ ሰዎች የኢሜል መልእክት ከደረሰ በኋላ ነው።

ፎርቦስ መጽሄት ያገኘው የኤክስ ኢሜል እንደሚያሳየው በኩባንያው ውስጥ ያለ 'አትሀንድል' የተባለ ቡድን በተጠቃሚዎች የተተው አካውንቶችን ለመሸጥ ገበያ ፈጥሯል።

ኤክስ የመግዛት አቅም አላቸው ብሎ ለሚያስባቸው ሰዎች 50 ሺህ ዶላር ግዙ የሚል የኢሜል መልእክት የሚልክባቸው አጋጣሚዎችም አሉ ተብሏል።

ፎርስ የተቀባዮችን ደህንነት ለመጠበቅ በማሰብ ለማን እንደተላኩ ሙሉ በሙሉ ያልገለጻቸው እነዚህ የኢሜል መልእክቶች የተላኩት ከኩባንያው ሠራተኞች ነው።

ኩባንያው በሚሸጥበት 'ሀንድል' ላይ ያሉ ደንብ እና መመሪያዎችንም አሻሽሏል።



የኤክስ ባለቤት ኢለን መስክ እንዲህ አይነት አቅድ ወደ ተግባር ያስገባል የሚል አሉባልታ ለወራት ሲወራ ቆይቷል

የኤክስ ባለቤት ኢለን መስክ እንዲህ ዓይነት አቅድ ወደ ተግባር ያስገባል የሚል አሉባልታ ለወራት ሲወራ ቆይቷል።

መስክ በፈረንጆቹ 2022 በመጀመሪያ ላይ በማህበራዊ ሚዲያ ገጹ ብዙ ቁጥር ያላቸው አካውንቶችን መሰብሰቡን እና የአርትኦት ሥራ እንደሚሰራባቸው መግለጹ ይታወሳል።

የኤክስ 'ኢንአክቲቭ አካውንት ፖሊሲ' እንደሚለው ከሆነ ተጠቃሚዎች 'ኢንአክቲቭ' ተደርገው እንዳይቆጠሩ በየ30 ቀናቱ ወደ አካውንታቸው መግባት ይጠቅባቸዋል።

ኤክስ በአሁኑ ወቅት 'ኢንአክቲቭ' የሆኑ አካውንቶችን ዝርዝር አልለቀቀም ሲል የዘገበው አል ዓይን ነው።

## የዓለማችን ረጅሙ ሰው ሕይወቱ አለፈ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በአንድ ወቅት የዓለማችን ረጅሙ ሰው የነበረው ፓኪስታናዊው ጉላም ሻቢር ሕይወቱ እንዳለፈ ተገልጿል፡፡

ከፈረንጆቹ 2000 እስከ 2006 ድረስ የዓለማችን ረጅሙ ሰው ተብሎ በዓለም የድንቃ ድንቅ መዝገብ ላይ ስሙ ተመዝግቦ የነበረው ሻቢር በልብ ህመም ምክንያት ሕይወቱ አልፏል፡፡


በሳውዲዋ ጅዳህ ከተማ ይኖር የነበረው ጉላም ሻቢር ለዓመታት በልብ ህመም ሲሰቃይ እንደነበርም ተገልጿል፡፡

ሻቢር በሕይወት ዘመኑ 42 ሀገራትን እንደጎበኘ የገለጸ ሲሆን ሳውዲ አረቢያ ለእርሱ ምርጧ ሀገር ናት በሚል እስከ ሕይወት ዘመኑ ድረስ ሲኖር ነበርም ተብሏል፡፡

በ1980 በፓኪስታን የተወለደ ሲሆን ቁመቱ ሁለት ነጥብ 55 ሜትር ርዝመት መድረሱን ተከትሎ ለስድስት ዓመታት የዓለማችን ረጅሙ ሰው ተብሏል።

ቱርካዊው ሱልጣን ኮሰን አሁን ላይ የዓለማችን በሕይወት ያለ ረጅሙ ሰው ሲሆን ቁመቱም ሁለት ነጥብ 51 ሜትር ርዝመት አለው፡፡

አሜሪካዊው ሮበርት ዋድሎው በሁለት ነጥብ ሰባት ሜትር በሰው ልጆች ታሪክ ረጅሙ ሰው ተብሎ በዓለም ድንቃ ድንቅ መዝገብ የሰፈረ ሲሆን በ1940 ሕይወቱ እንዳለፈ ተገልጿል ሲል አል ዓይን ዘግቧል።



ዜና

# የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ግብይት ሦስት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር የሚሸፍኑ ሲሆን፤ በመጠን 25 ሺህ 239 ሜትሪክ ቶን ናቸው ብለዋል።

ምርት ገበያ የግብይት ሥርዓቱንና አገልግሎቱን በማሻሻል አርሶ አደሩ፣ አቅራቢው፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራትና ላኪዎችን በማገልገል ላይ ነው ያሉት አቶ በኃይሉ፤ ሀገሪቱ ከውጭ ምንዛሬ የምታገኘውን ገቢ ለማሳደግ ጥረት እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከሚደረገው ጥረት ውስጥ የበይነ መረብ ግብይት ማስጀመር፤ ተጨማሪ የግብርና ምርቶችን ወደ ግብይት ሥርዓቱ ማስገባት መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም በግብይት ሥርዓቱ ውስጥ የሚገኙትን ምርቶች መጠን መጨመር እንዲሁም የመጋዘን ደረሰኝና የብድር አገልግሎትን ማስፋት ተጠቃሽ ናቸው ብለዋል።

የዘንድሮ በጀት ዓመት ሲጠናቀቅ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ 37 ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸው 423 ሺህ 859 የተለያዩ ምርቶችን ለማገበያየት እየተሠራ ነው ያሉት አቶ በኃይሉ፤ ምርት ገበያው በ2015 በጀት ዓመት 24 ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸውን 257 ሺህ ሜትሪክ ቶን የተለያዩ ምርቶችን ማገበያየት መቻሉን አንስተዋል።

በአለፈው ዓመት ግብይት ከተፈጸመባቸው 257 ሺህ ሜትሪክ ቶን ምርቶች መካከል 75 ሺህ ሜትሪክ ቶኑ የአኩሪ አተር ምርት መሆኑን አውስተዋል። 62 ሺህ ሜትሪክ ቶን የሰሊጥ እንዲሁም 57 ሺህ ሜትሪክ ቶኑ የቡና ምርቶች ግብይቱ የተፈጸመ ሲሆን ቀሪውን የግብይት መጠን በሌሎች ምርቶች እንደተሸፈነ ኃላፊው አስታውቀዋል።

# ትርጉም የሚያስፈልጋቸው 10...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ጽሕፈት ቤት አስታወቀ፡፡

የጽሕፈት ቤቱ ኮሙኒኬሽን ቢሮ ተጠባባቂ ዳይሬክተር ወይዘሮ ይርጋለም ጥላሁን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ጉባዔው በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት 504 መዝገቦችን ተመልክቷል፡፡

ከተመለከታቸው መዝገቦች መካከል የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልጋቸው 10 መዝገቦችን የለየ ሲሆን፤ መዝገቦቹን የሕገ መንግሥት ትርጉም ለማሰጠት ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ልኳል ብለዋል፡፡

ጉባዔው ለተከማቹ አቤቱታዎች ምላሽ ለመስጠት ካለፉ ጊዜያት በተለየ ሁኔታ ሲሠራ ቆይቷል ያሉት ወይዘሮ ይርጋለም፤ በዚህም ካለፉት በጀት ዓመታት አኳያ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የባለጉዳይ አቤቱታዎች መመልከት መቻሉን ነው የተናገሩት፡፡

በሦስት ወራት ውስጥ የታየው የመዝገብ ብዛት ከዚህ ቀደም በአንድ ዓመት ውስጥ ማስተናገድ እንደማይቻል አንስተው፤ በተሠራው ሥራ ባለፈው ሩብ ዓመት በጽሕፈት ቤቱ የነበረውን የአቤቱታ ክምችት መቀነስ እንደተቻለ አመላክተዋል፡፡

ጉባዔው የተመለከታቸው መዝገቦች ቁጥር ከፍተኛ ቢሆንም የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ሆነው የተገኙ መዝገቦች ቁጥር አነስተኛ መሆኑን የገለጹት ተጠባባቂ ዳይሬክተሯ፤ ይህ ሊሆን የቻለው ኅብረተሰቡ አጣሪ ጉባዔውን እንደ መጨረሻ የፍትህ አማራጭ አድርጎ እየወሰደው በመምጣቱ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ጉባዔው የቀረቡለትን መዝገቦች በሙሉ የመመርመር ግዴታ የተጣለበትና ግዴታውንም እየተወጣ ያለ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሆኖም በኅብረተሰቡ ዘንድ የግንዛቤ ክፍተቶች እንዳሉ ጠቁመዋል። የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያሻቸውና አጣሪ ጉባዔውን የሚመለከቱ ጉዳዮች ብቻ መቅረብ ሲገባቸው፤ ሕገ መንግሥታዊ ያልሆኑ ጉዳዮች ለጉባዔው እየቀረቡ መሆናቸውንም ለአብነት አንስተዋል፡፡

ለዚህም ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራዎች እየተሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

ጉባዔው እስከያዝነው በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ሌሎች የተከማቹ መዝገቦችን የማጥራት ሥራዎችን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ዳይሬክተሯ ገልጸዋል፡፡

ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች ብቻ ወደ ጉባዔው እንዲመጡ አሳስበው፤ ጉባኤው ኅብረተሰቡ መብቱን ለማስከበር በሕግ ዙሪያ ያለውን ግንዛቤ እንዲያሳድግ የሚያግዙ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን እንደሚያዘጋጅም ተናግረዋል፡፡

# «አካዳሚው በአህጉር ደረጃ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሚያስችላቸውን ስምምነት ተፈራርመዋል።

ስምምነቱን የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ርዕሰ አካዳሚ አቶ ዛዲግ አብረሃና የቻይና ብሔራዊ አስተዳደር አካዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት ጎንግ ዌቢን (ፕ/ር) ፈርመዋል።

በወቅቱ አቶ ዛዲግ አብረሃ እንደተናገሩት፤ በአፍሪካ ውስጥ ላለው ድህነትና የእርስ በእርስ ግጭት ዋነኛው ምክንያት የአመራር ችግር በመሆኑ አካዳሚው ችግሩን ለመፍታት ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል።

አካዳሚው የአፍሪካ ኅብረትን ጨምሮ ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ጋር ስምምነት በመፍጠር የተለያዩ ሥልጠናዎችን ለመስጠት የሚያስችል ሥራ እያከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል።

የአካዳሚው ሥራ በኢትዮጵያ ብቻ የታጠረ አይደለም ያሉት አቶ ዛዲግ፤ አፍሪካ ያላትን የማደግ አቅም በአግባቡ እንድትጠቀም በአህጉሪቱ ያለውን የአመራር ችግር ለመቀነስ የሚረዳ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ርዕሰ አካዳሚው አመልክተዋል።

ተቋሙ በመላው አፍሪካ የመሥራት ፍላጎት እንዳለው ያነሱት አቶ ዛዲግ፤ ከቻይናው አካዳሚ ጋር የተደረሰው ስምምነት ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት የሚረዳ ነው ብለዋል።

አካዳሚው ብቁ አመራሮችን ለማፍራት እያከናወነ በሚገኘው ሥራ ከቻይና በርካታ ተሞክሮዎችን መውሰድ እንደሚችል ገልፀው፤ በኢትዮጵያ በሁሉም መስክ ብቁና ጠንካራ አመራሮችን ለማፍራት አካዳሚው ጠንክሮ በመሥራት ላይ መሆኑን ጠቁመዋል።

አካዳሚው መሪዎችን ለማብቃት ከሚሠራው ሥራ በተጨማሪ ተቋሙን ይበልጥ ለማዘመን በሚደረገው ጥረት ከሌሎችም ተቋማት በሚገኝ እገዛ አማካኝነት የተለያዩ መሠረተ ልማቶች እየተሟሉ መሆኑን ርዕሰ አካዳሚው አብራርተዋል፡፡

እንደ አቶ ዛዲግ ገለጻ፤ ከቻይናው አካዳሚ ጋር የተደረሰው ስምምነቱ የሁለቱን ተቋማት ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር የኢትዮጵያ ከፍተኛ አመራሮች በሥልጠና፣ በምርምርና በማማከር ተገቢውን ድጋፍ እንዲያገኙና በአፍሪካ ለመሥራት የታቀዱ ሥራዎችን በተጠናከረ መልኩ ማከናወን የሚያስችል ድጋፍ የሚገኝበት ነው።

የቻይና ብሔራዊ አስተዳደር አካዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት ጎንግ ዌቢን (ፕ/ር) በበኩላቸው፤ የአካዳሚዎቹ ስምምነት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና የቻይናው ፕሬዚዳንት ሺ ጂፒንግ በቅርቡ ከተካሄደው የብሪክስ ጉባኤ ጎን ለጎን ያደረጉት ስምምነት አካል መሆኑን አስታውቀዋል።

በስምምነቱ መሠረት በሁለቱ አካዳሚዎች መካከል የአመራር ልማት፣ የፕሮጀክት ግንባታ፣ የባለሙያዎች ልውውጥ፣ የአካዳሚክ ሀብቶች ድጋፍ፣ በጥናት፣ በምርምርና በሌሎች ዘርፎች ላይ በጋራ ይሠራሉ ብለዋል።

የተደረገው ስምምነት በሁለቱ አካዳሚዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ከፍ ያደርገዋል ያሉት ፕሮፌሰር ጎንግ፤ የቻይና ብሔራዊ አስተዳደር አካዳሚ በአመራር ልህቀት ዘርፍ ያለውን ልምድና ተሞክሮ ለኢትዮጵያ ለማካፈል ዝግጁ መሆኑን ገልፀዋል።

# አማራ ክልል

በከሳሽ አስማረ አዱኛ እና በተከሳሽ ታምራት በላይ አለሙ መካከል ስላለው የገንዘብ ክስ ተከሳሾች ባድራሻቸው የፍርድ ቤት መጥሪያ ተልኮላቸው በቀጠሮ ቀን ሊቀርቡ ስላልቻሉ ለቀጠሮው ለ11/03/2016 ዓ.ም በ2፡30 ሰዓት ደቡብ ጐንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት 1ኛ ችሎት ድረስ እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን ጉዳዩ ተከሳሾች በሌሉበት የሚታይ መሆኑን ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት የደ/ጎን/አስተዳደር**
**ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት**

# አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ/አመልካች /ፍ/ባለመብት 1ኛ ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ እና በተከሳሽ/ተጠሪ/ባለዕዳ 1ኛ ከታ ከቻ ዲንቃ ህንፃ ስራ ተቋራጭ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 1ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በፅሁፍ ለ10/03/2016 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት 12/3/2016 ዓ.ም በ4፡30 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች/ፍ/ባለመብት 1ኛ ንብ ኢንሹራንስ ኩባንያ ኢ.ማ እና በተከሳሽ/ተጠሪ/ባለዕዳ 1ኛ ባንቿ አምላክ መከተ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ከሳሽ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 3ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በፅሁፍ ለ04/03/2016 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ሰዓት ይዘው እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች ንብ ኢንሹራንስ ኩባንያ ኢ.ማ እና በተከሳሾች/ተጠሪዎች 1ኛ አቶ አለቤ አጅሎ፣ 2ኛ አቶ ሳሙኤል ሞላ ካሳ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሾች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 2ኛ ባንክ ኢንሹራንስ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በፅሁፍ ለ18/03/2016 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት ለ20/03/2016 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ መልስ ካልቀረበ መዝገቡ ለችሎት የሚቀርብ ይሆናል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች/ፍ/ባለመብት 1ኛ ህብረት ኢንሹራንስ ኩባንያ እና በተከሳሾች/ተጠሪዎች/ባለዕዳዎች 1ኛ አቶ ቴዎድሮስ ደሳለኝ፣ 2ኛ አቶ አማን ተስፋሁነኝ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 3ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በፅሁፍ ለ06/03/2016 ዓ.ም በ8፡00 ሰዓት ይዘው እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች/ፍ/ባለመብት 1ኛ ሉሲ ኢንሹራንስ ኢ.ማ እና በተከሳሾች/ተጠሪዎች/ባለዕዳዎች 1ኛ ጳውሎስ አለሙ፣ 2ኛ አብዶ መኮንን በዳዳ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 4ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በፅሁፍ ለ04/03/2016 ዓ.ም በ8፡00 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት 06/3/2016 ዓ.ም በ8፡00 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች/ፍ/ባለመብት 1ኛ ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ እና በተከሳሽ/ተጠሪ/ባለዕዳ 1ኛ ብርሃኑ ታደሰ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 2ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በፅሁፍ ለ19/03/2016 ዓ.ም በ8፡20 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት 24/03/2016 ዓ.ም በ4፡30 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች/ፍ/ባለመብት 1ኛ ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ እና በተከሳሽ/ተጠሪ/ባለዕዳ 1ኛ ወርቅነሽ ጌታቸው መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 2ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በፅሁፍ ለ19/03/2016 ዓ.ም በ8፡25 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት 24/3/2016 ዓ.ም በ4፡40 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች ኢትዮ ቴሌኮም እና በተከሳሽ/ተጠሪ ሔለን ሐብታሙ ጓደኞቻቸው ኃላ/የተ/የግ/ማ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ኢ ምድብ 1ኛ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች/ ተጠሪዎች በ07/03/2016ዓ.ም በ3፡45 ሰዓት በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

በከሳሽ አምሳሉ ሚሊኪያስ እና በተከሳሾች ትዕግስት አስፋው መካከል ስላለው የፍ/ብሄር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ መከሰስዎን አውቀው ለ20/3/2016 ዓ.ም በ3፡00 ሰዓት የተቀጠረ መሆኑን አውቀው በፌ/ከ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 4ኛ ፍ/ብሔር ቀጥታ ክስ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ የማይቀርቡ ከሆነ ጉዳያችሁ በሌላችሁበት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

ከሳሽ/አመልካች አቶ ኡብሳ ኢብራሂም አሊ እና ተከሳሾች/ተጠሪዎች 1. ማፋ ጠቅላላ የህንፃ ተቋራጭ ሀ/የተ/የግ/ማ፣ 2. አቶ መስፍን ፍልታሶ ዳአ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 9ኛ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በ10/03/2016ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ/አመልካች የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና በተከሳሾች/ተጠሪዎች 1ኛ. ዳሚ የጽዳት አገልግሎት ኃ/የተ/የግ/ማ፣
2ኛ. አቶ አለማየሁ ዜና፣
3ኛ. ኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ ኢ.ማ
መካከል ስላለው የፍትሐብሄር ክርክር ጉዳይ ከሳሽ ፍ/ቤቱ በሰጠው እትዛዝ ተከሣሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 3 ባ/ኢንሹራንስ ችሎት እየታየ መሆኑነ በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ በ14/3/2016 ዓ.ም 8፡10 ሰዓት ይዘው እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

# ስፖርት





# ከ15 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን በሴካፋ የመጀመሪያውን ድል አስመዘገባል

ዓስማየሁ ግዛው

የኢትዮጵያ ከ15 ዓመት በታች የወንዶች እግር ኳስ ብሔራዊ ቡድን የምድቡን ሁለተኛ ጨዋታ ከትላንት በስትያ ከጅቡቲ ጋር አድርጎ በፍፁም የበላይነት 8ለ1 በማሸነፍ የመጀመሪያ ድሉን ማስመዝገብ ችሏል፡፡

ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ እየተሳተፈችበት የምትገኘው የሴካፋ ከ15 ዓመት በታች የታዳጊ ወንዶች እግር ኳስ ውድድር ከጥቅምት 24/2016 ዓ.ም ጀምሮ በዩጋንዳ አስተናጋጅነት እየተካሄደ ይገኛል፡፡

ስምንት ቡድኖች ጠንካራ ፉክክር እያደረጉበት በሚገኘው በዚህ ውድድር ኢትዮጵያ የጅቡቲ አቻዋን ከግማሽ ደርዘን በላይ ግብ በማስቆጠር ስታሸንፍ ስድስት ተጫዋቾች አንድ አንድ ጎል አስቆጥረዋል። አንድ ተጫዋች ደግሞ ሁለት ግቦችን አስቆጥሯል፡፡ ብሔራዊ ቡድኑን የወከሉት ወጣቶች በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን እና በጀርመኑ ስሪ ፖይንትስ ተባባሪነት በካፍ አካዳሚ ውስጥ የእግር ኳስ ስልጠናቸውን እየወሰዱ የሚገኙና እድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊዎች የተካተቱበት መሆኑ ይታወቃል። በዚህም የዕድሜ እርከናቸውና ሜዳ ላይ ባሳዩት ማራኪ እንቅስቃሴ ትልቅ ተስፋ አሳይተዋል፡፡

በመጀመሪያው የምድብ ጨዋታቸው ደቡብ ሱዳንን በመግጠም 1 ለ 1 በሆነ አቻ ውጤት የተለያዩት እነዚህ ታዳጊዎች በውድድሩ ጥሩ ውጤት ያስመዘግባሉ ተብሎም ተስፋ ተደርጎባቸዋል።

ተስፈኞቹ ታዳጊዎች በጅቡቲው ጨዋታ የጎል አካውንታቸውን በሁለተኛው ደቂቃ በመከፈት ይሁን ካሳሁን ከመረብ ባሳረፋት ግብ መምራት ችለዋል፡፡ ኢትዮጵያ የጨዋታ የበላይነቷን በማስቀጠል በርካታ ሙከራዎችን እያደረጋች ጫና ፈጥራ በመጫወት በ10ኛው ደቂቃ ሙእተሲምቢላ ፋሲል በተሰራበት ጥፋት የተገኘውን የፍፁም ቅጣት ምት ተጠቅሞ ግሩም ግብ በማስቆጠር የቡድኑን መሪነት ወደ 2 ለ 0 ከፍ ማድረግ ችሏል፡፡ ታዳጊዎቹ ተደጋጋሚ የሆነ የጅቡቲን የጎል ክልል በማንኳኳት በ22ኛው ደቂቃ ከመሃል ሜዳ ጀምሮ ባደረጉት ድንቅ ቅብብል ወደ ፍፁም ቅጣት ምት ክልል ገብቶ በመስፍን መላ ሶስተኛ ጎላቸውን አግኝተዋል። ማራኪና ተስፋን የሚያጭር እንቅስቃሴን ማስመልከት የቻሉት ወጣቶቹ ተስፈኞች 3 ለ 0 እየመሩ ለእረፍት ወደ መልበሻ ክፍል አምርተዋል፡፡

ከእረፍት መልስ ጥሩ የሆነ እንቅስቃሴን ማሳየት የቻሉት ወጣቶች በ55ኛ ደቂቃ ላይ የጨዋታውን አራተኛ ጎል በኦዳ መሐሙድ አማካኝነት በማስቆጠር መሪነታቸውን አጠናክረው የማሸነፍ እድላቸውን ማስፋት ችለዋል፡፡ ተጨዋቹ ከመሃል ሜዳ የተላከለትን ኳስ በአየር ላይ አክርሮ በመምታት የጅቡቲውን ግብ ጠባቂ እግሮች አልፋ ከመረብ ልትገናኝ ችላለች፡፡ በሁለተኛ አጋማሽ ተቀይሮ ወደ ሜዳ የገባው ናትናኤል ላራንጎ በ77 ደቂቃ ከመሃል ሜዳ የተሻማለትን ኳስ በአስገራሚ ሁኔታ በጭንቅላቱ በመግጨት ከመረብ በማሳረፍ የቡድኑን መሪነት ወደ 5 ጎሎች አሳድጓል፡፡ ከሁለት ደቂቃዎች በኋላ አሌክስ ዳሮ ከመስፍን መላ የተሻገረለትን ኳስ ብቻውን አግኝቶ የጎል መጠኑን ወደ 6 አድርሶታል፡፡ ማሸነፋቸውን እያረጋገጡ የመጡት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ተስፈኞች በመስፍን መላ በ88ኛው ደቂቃ ለቡድኑ ሰባተኛ ለራሱ ሁለተኛ ጎል ማስቆጠር ችሏል፡፡ መደበኛው የጨዋታ ሰዓት ተጠናቆ በተጨመረው የባከነ ሰዓት አብነት ማርቆስ ስምንተኛዋንና የማሳረጊያዋን ጎል በማስቆጠር ጨዋታው በኢትዮጵያ ታዳጊዎች ብሔራዊ ቡድን 8 ለ 1 አሸናፊነት ተጠናቋል፡፡ ጅቡቲዎችን ከመሸነፍ ያልታደገቻቸውን አንድ ግብ ከማዕዘን ምት የተሻማውን ኳስ አብዲ ሳዲቅ አስቆጥሯል። ኢትዮጵያ ታዳጊዎች ብሔራዊ ቡድን በሙሉ የጨዋታ ሰዓት በሁሉም የእግር ኳስ መለኪያዎች የተሻለና ተስፋን የሚያጭር እንቅስቃሴን በማድረግ ጨዋታውን መጨረስ ችሏል፡፡

ብሔራዊ ቡድኑ የምድቡን የመጨረሻ ጨዋታ ነገ ከጠንካራዋ ዩጋንዳ ጋር በማድረግ የሚያጠናቅቅ ሲሆን ጠንከር ያለ ፈተና እንደሚገጥመውም ይጠበቃል፡፡ በመጀመሪያው ጨዋታቸው ጅቡቲን ገጥመው 15 ለምንም ያሸነፉት ኡጋንዳዎች በሁለተኛ ጨዋታቸው ደቡብ ሱዳንን 3 ለ ምንም ረተው ምድቡን በበላይነት እየመሩ ኢትዮጵያን ይገጥማሉ፡፡

ኢትዮጵያ በምድብ አንድ ከዩጋንዳ፣ ጅቡቲና ከደቡብ ሱዳን ተደልድላ ውድድሯን እያደረገች ሲሆን ታንዛኒያ ዛንዚባር፣ ሶማሊያ እና ሩዋንዳ በምድብ ሁለት ተደልድለው ውድድራቸውን በማድረግ ላይ የሚገኙ ሀገራት ናቸው፡፡ ውድድሩ ለመጀመሪያ ጊዜ እአአ በ2019 ዓ.ም በኤርትራ መዲና አስመራ ተካሂዶ የውድድሩ የመጀመሪያ አሸናፊ የአሁኗ አስተናጋጅ ሀገር ዩጋንዳ ነበረች፡፡ ውድድሩ እስከ መጨረሻ እጅግ ከፍተኛ ፉክክርን እንደሚያስተናግድ ሲጠበቅ በሚቀጥለው ዓመት በዞን ደረጃ ለሚካሄደው የአፍሪካ ከ17 ዓመት በታች ውድድር የሚለዩበት እንደሚሆን የውድድሩ አዘጋጆች ገልጸዋል፡፡